# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 240 ሚያዝያ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ግብርናውን ለማዘመንና ምርታማነቱን ለማሳደግ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተዋል

- ከቤተ ሙከራ ወደ አዝመራ የተሰኘ የግብርናና ሳይንስ አውደርዕይ ተከፈተ

ጌትነት ምህረቴ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አዲስ አበባ፡- ግብርናውን ለማዘመንና ምርታማነት ለማሳደግ የተጀመሩ ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስፋት ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ “ከቤተ ሙከራ ወደ አዝመራ” በሚል መሪ ቃል በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የግብርና ሳይንስ አውደ ርዕይ ትናንት መርቀው ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ ግብርና ከሰዎች ህይወት ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ግብርናውን በቴክኖሎጂ በመደገፍ እና በእንስሳት፣ በማር፣ በቡና፣ በስንዴና በሌሎች ምርቶች ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች

ግብርናውን ለማዘመንና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ የአገርን ነጻነት ከማስጠበቅ ጋር የተያያዘ ነው”

- አቶ ደመቀ መኮንን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- የግብርና ምርታማነትን የማሳደግ ጉዳይ በምግብ ራስን ከመቻል ባለፈ ከአገርና ከኢኮኖሚ ነጻነት ጋርም ጭምር የሚያያዝ መሆኑን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለጹ፡፡

አቶ ደመቀ መኮንን በሳይንስ ሙዚየም “በስንዴ የተገኘውን ስኬት በሌሎችም ምርቶች መድገም” በሚል መሪ ቃል ባስጀመሩበት የፓናል ውይይት ላይ እንዳሉት፤ የግብርና ምርታማነት ማሳደግ ቀዳሚ አጀንዳችን ሊሆን ይገባል፡፡ ምክንያቱም የግብርና ምርታማነትን የማሳደግ ጉዳይ በምግብ ራስን ከመቻል ባለፈ ከአገርና ከኢኮኖሚ ነጻነት ጋር ጭምር የሚያያዝ ነው፡፡

ግብርና የእድገት ምንጭ፣የአብዛኛው ህዝባችን የኑሮ መሰረት

“የግብርና ምርታማነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## “ትውልዱ የሚያነብ፣ ነገሮችን በትኩረት የሚያይና የሚያዳምጥ ሲሆን አሁን ካለችው የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላለን”

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- "ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ" የመጻሕፍት አውደ ርዕይ ማጠቃለያ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ትውልዱ የሚያነብ፣ ነገሮችን በትኩረት የሚያይና የሚያዳምጥ ሲሆን አሁን ካለችው የተሻለች ኢትዮጵያን መፍጠር እንችላለን ሲሉ ተናገሩ።

ትውልዱ የሚያነብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የአእምሮ ጤና በህብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ጫና እየጨመረ ነው

ገጽ 2

## የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በፖሊሲና በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘላቂነት ይቀጥላል

ገጽ 4






















ዜና



አቶ አህመድ አብዱልቃድር

## በአፋር ክልል ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የቱሪዝም እንቅስቃሴው መነቃቃት እያሳየ ነው

### - ከአንድ ሺህ 200 በላይ የውጭ አገር ቱሪስቶች ክልሉን ጎብኝተዋል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በአፋር ክልል ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የቱሪዝም እንቅስቃሴው ከፍተኛ መነቃቃት እያሳየ እንደሆነ የክልሉ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ። ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአንድ ሺህ 200 በላይ ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸው ታውቋል።

የአፋር ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ አብዱልቃድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ሁለት እና ሦስት ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ በነበረው ጦርነት የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ እስከመዘጋት የደረሰ መሆኑን አስታውሰው፤ አሁን ላይ በተፈጠረው ሰላም የቱሪዝም ኢንዱስትሪው እያንሰራራ እንደሆነ ተናግረዋል።

በ2012 እና 2013 ዓ.ም ተቋርጦ የነበረው የክልሉ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ባለፈው ዓመት በመጠኑ ተከፍቶ 34 የውጭ አገር ቱሪስቶች ክልሉን እንደጎበኙ የተናገሩት አቶ አህመድ፤ በዚህ ዓመት ከፍተኛ መነቃቃት በማሳየት አንድ ሺህ 260 የውጭ አገር ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸውን ገልጸዋል።

ባለፉት ዘጠኝ ወራት አንድ ሚሊዮን 260 ሺህ ብር ከቱሪዝም መዳረሻዎች የመግቢያ ክፍያ መሰብሰቡን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ ከቱሪዝም እንቅስቃሴው 11 ሚሊዮን 41 ሺህ 940 ብር ገቢ እንደተገኘ ተናግረዋል።

የነበረው ጦርነት ቱሪዝሙን በእጅጉ ጎድቶት እንደነበር የሚናገሩት አቶ አህመድ፤ የሰላም ስምምነቱ በፍጥነት መተግበሩ ለውጭ አገር ቱሪስቶች ትልቅ ዋስትና በመስጠቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የውጭ አገር ጎብኚዎች ክልሉን ለመጎብኘት እየመጡ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ክልሉ የቱሪስቶችን ሰላም እና ደህንነት ለመጠበቅ የጸጥታ አካላትን በማቀናጀት ጎብኚዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ የሚፈልጉትን ቦታ ጎብኝተው እንዲመለሱ የማድረግ ስራዎችን እየሰራ ነው።

የቱሪስት መዳረሻዎችን በማልማት ለቱሪስት ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ሲሆን፤ ሞተር አልባ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን በዳሎል እና በኤርታሌ የመሞከር ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነም ተናግረዋል።

ክልሉ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት የማስተዋወቅ ስራዎች እየተሰራ እንደሆነ የጠቆሙት አቶ አህመድ፤ በጅቡቲ በኩል ለሚመጡ ጎብኚዎች ለቱሪስት ቪዛ በሩ ክፍት እንዲሆን እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት የሚደረጉት የገበታ ለሀገር እና ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክቶች በቀጣይ በአፋር ክልል እንደሚጀመሩ ተናግረው፤ ይህም ለክልሉ የቱሪዝም እድገት የራሱ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

አፋር ያልተነኩ ድንቅ የተፈጥሮ መስህቦች መገኛ መሆኑን እንዲሁም የሉሲ፣የዳሎል፣የኤርታሌ እና የአዋሽ ወንዝ ማስረጊያ የሆነው አቤይ ሀይቅ መገኛ መሆኑን አስታውሰው፤ የአገር ውስጥ እና የውጭ ቱሪስቶች ክልሉን እንዲጎበኙ ጥሪ አስተላልፈዋል።

# የአእምሮ ጤና

## በህብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ጫና እየጨመረ ነው

**እፀገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ፡- የአእምሮ ጤና በህብረተሰቡ ላይ እያደረሰ ያለው ጫና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ የሬናሰንት የአእምሮ ጤና እና የሱስ ተሃድሶ ማዕከል በተመረቀበት ወቅት እንዳሉት፤ በአሁኑ ወቅት የአእምሮ ጤና ችግር እየሰፋ በመምጣቱ ቅድሚያ ከሚሠጣቸው የህብረተሰብ የጤና ችግሮች ውስጥ የተካተተ ሆኗል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በተለይም በአእምሮ ጤና እና ሱስ ህክምና ዙሪያ መስራት ማህበራዊ ሀላፊነትን መወጣት በመሆኑ በዘርፉ የሚሰሩ ስራዎችን በሙሉ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያደንቃል፣ ይደግፋልም ብለዋል።

የአእምሮ ጤና ችግር የህብረተሰብ የጤና ችግር ውስጥ ተካትቶ የራሱ አገር አቀፍ ስትራቴጂክ እቅድ ኖሮት በተለይም መከላከልና የህክምና ተደራሽነቱ እንዲጠናከር በመጀመሪያ ደረጃ ተቋማት እንዲሰጥ ስራዎች እየተሠሩ መሆናቸው ገልጸዋል።

ከዚህ አንፃር በተለይ የሱስ ህክምናና ተሀድሶ እጅግ ትኩረት የሚሻ በተለይ ወጣትና አምራች ማህበረሰቡን እያጠቃ ያለ ችግር መሆኑን የገለጹት ዶክተር ሊያ፤ ይህን ችግር ከመቅረፍ አንጻር የሬናሰንት የአእምሮ ጤናና የሱስ ተሃድሶ ማእከል የህክምና አገልግሎቱን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ገልፀዋል።

በአእምሮ ጤና እና ሱስ ችግር ህክምና ላይ ኢንቨስት ማድረግ ችግሩ ላለባቸው ህሙማን አማራጭ ህክምና መስጠት መሆኑን የገለጹት ዶክተር ሊያ፤ በተለይ ለአእምሮ ጤና ችግር አጋላጭ የሆኑ መንስኤዎች ለምሳሌ የአደንዛዥ ዕጽና አነቃቂ ነገሮች ተጠቃሚነትን ለመከላከል የሁሉም ማህበረሰብ ርብርብ ይጠይቃል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት የአደንዛዥ እፆች ዝውውርና ተጠቃሚነት ሁኔታ እየተስፋፋ መምጣቱን ተከትሎ በቂ ግንዛቤ ባልተፈጠረላቸውና ሁሉንም ነገር ለመሞከር በሚጓጉት ወጣቶችና ታዳጊዎች ስብዕና ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እያሳደረ እንደሚገኝ የገለጹት ደግሞ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ናቸው።



እንደ ዶክተር ኤርጎጌ ገለጻ፤ እስካሁን የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነትንና ሱሰኝነትን ለመከላከል የሚረዱ ጥረቶች በተለያዩ አካላት የተጀመሩ ቢሆንም ከችግሩ ስፋትና ግዝፈት አንጻር ግን በቂ አይደሉም፤ በመሆኑም ቅንጅታዊ አሰራርን ማዕከል ባደረገ መልኩ ስራዎች ሊከናወኑ ይገባል ብለዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር ሀገራዊ ግብረ ሀይል በማቋቋምና ስትራቴጂክ እቅድ በማዘጋጀት የወጣቶችና ታዳጊዎችን ስብዕና ከመገንባት ጎን ለጎን አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ አደንዛዥ እፆችን ለመከላከል የሚያስችል ተግባራትን ለማከናወን ግብ ተጥሎ ወደ ስራ መገባቱንም አብራርተዋል።

የሬናሳንት አእምሮ ጤና እና የሱስ ተሃድሶ ማእከል መስራች የሆኑት ፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ፤ ማእከሉ የተለያዩ የአእምሮ ጤና ምርመራና ህክምና፣ የላብራቶሪ፣ የምክር አገልግሎትና የተኝቶ እና ተመላላሽ ህክምና አገልግሎቶችን እንደሚሠጥ ጠቁመው፤ እስከ አሁንም 25 አልጋዎችን በማዘጋጀት የሱስ ችግር ውስጥ ያሉ ወጣቶችን በማገዝ ላይ መሆኑን አብራርተዋል።

# ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በጥናትና ምርምር ዝርያዎችን በማሻሻል ውጤታማ ሥራዎችን ሠርቷል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማር ስራው በተጨማሪ በምርምር የተሻሻሉ ዝርያዎችን በመጠቀም የፍራፍሬ፣ የእንሰት፣ የቡናና የእንስሳት እርባታ ላይ ተሰማርቶ ውጤታማ ስራዎችን በማከናወን ላይ እንደሚገኝ አስታወቀ።

በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ከለለው አዲሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ቦንጋ ዩኒቨርሲቲ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ባለሙያዎችን በማሰማራት ችግር ፈች የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማከናወን በአካባቢው ያሉትን ችግሮች በመፍታት ላይ ይገኛል።

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ከ60 በላይ የሚሆኑ የጥናትና ምርምር ፕሮጀክቶች ላይ 40 የሚደርሱ ጥናቶች ተሰርተው እንደተጠናቀቁ የገለጹት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በተያዘው ዓመት 19 የምርምር ስራዎች በዓለም አቀፍ ጆርናል ላይ እንደታተሙ ገልጸዋል። ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ በተለየ መልኩ ቀጣይነት ያላቸውን 14 የምርምር ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሚገኙ ዶክተር ከለለው ተናግረዋል።

ከአካባቢው ተፈጥሮአዊ ሀብት ጋር በተያያዘ አብዛኛው ማህበረሰብ ህይወቱን በግብርና እንደሚመራ ያስታወሱት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ይህንን በጥናትና ምርምር በመደገፍ በአካባቢው ያለው ሀብት ላይ በመስራት ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ከተፈጥሮ ሀብት ማህበረሰቡ መጠቀም ባለበት ልክ ጥቅም አላገኘም ይህንንም ለማሻሻል ከአካባቢው አየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የቡና ዝርያዎችን የማስፋፋት ስራ ተሰርቷል ነው ያሉት።



ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ከለለው አዲሱ

“ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የቡና ችግኞችን በማፍላት መትከል ተችሏል፤ በዚህ ዓመትም ሁለት ሚሊዮን ችግኞችን ለማፍላት የሚያስችል የቦታ ዝግጅት እየተደረገ ነው” ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ብቻ 84 ሄክታር መሬት በቡና ተሸፍኗል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ከለለው ገለጻ፤ የእንሰት ሰብል የምግብ ዋስትናን ከማስጠበቅ አኳያ ትልቅ ሚና አለው፤ አሁን ላይ ባለው ሁኔታ ማህበረሰቡ ወደ ሌሎች ዘርፎች ትኩረት በማድረጉ በጥናትና ምርምር በማስደገፍ የእንሰት ችግኞችን በግቢው ውስጥ በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ የማሰራጨት ስራ እየተሰራ ነው።

ዩኒቨርሲቲው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በሙዝ ልማት ላይ በስፋት በመስራት ውጤታማ እንደሆነ የገለፁት ዶክተር ከለለው፤ ይህም ሊሆን የቻለው ሙዝ በአካባቢው አይበቅልም የሚል አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ላይ በመኖሩ ይህንን እሳቤ ለመቅረፍ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም በማንጎ፣ አቮካዶ፣ አፕል፤ አናናስና ሌሎችም ላይ በመስራት ባለፈው ዓመት ከእነዚህ ምርቶች ሽያጭ ከ26 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንደተገኘና በተመጣጣኝ ዋጋ ለአካባቢው ማህበረሰብ ማቅረብ እየተቻለ እንደሆነ አብራርተው፤ በያዝነው ዓመት ከ39 ሚሊዮን በላይ ብር ለማግኘት እየተሰራ ነው ብለዋል።

በአካባቢው ለባህላዊ መድኃኒትነት የሚያገለግሉ የተለያዩ እፅዋት በመኖራቸው፤ በሽታዎችን በባህላዊ መንገድ የመፈወስ እውቀት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች በዞኑ እንደሚገኙ ጠቁመው። ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ የእፅዋት አይነቶችን በጋራ ለይቶ በማሰባሰብ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የባህላዊ መድኃኒት እፅዋት መጠበቂያና ማስፋፊያ ማዕከል ተከፍቶ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ ገልፀዋል።

ከ375 በላይ ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ እጽዋቶች በማዕከሉ እየተጠበቁ እንዳሉ የገለፁት ዶክተር ከለለው፤ ይህንን በቀጣይ ጊዜያት ከዘመናዊው ጋር በማዋሀድ ጠቀሜታውን ከፍ ለማድረግ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር እንዲሁም ከለንደን ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲ ጋር ስምምነት በመፍጠር እየተሰራ ነው ብለዋል።

በግቢው ውስጥ ከ13 በላይ ዝርያ ያላቸውን የቅመማ ቅመም አይነቶች በመትከል የምርምር ስራዎችን ለሚያከናውኑ ተመራማሪዎች ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤ ተግባር ተኮር ትምህርትን በማስፋፋት በገቢ ምንጭነት እያገለገለ እንደሚገኝ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በጤና፣ በብዝሀ ህይወትና በመሳሰሉት ዘርፊ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነ ጠቁመው፣ በእንስሳት ሀብት ልማት ዙሪያ የተለያዩ የምርምር ስራዎችን በመስራት የወተት ከብቶች፣ የበግ፣ የዶሮ እርባታ፣ የንብ ማነብና የስጋ ከብት ድለባ ላይ እየተሰራ ሲሆን 10 የንብ ማነብያ ጣቢያዎች ተዘጋጅተው ምርት እየተሰበሰበ ነው ብለዋል።



አቶ አመንቴ ጌሺ

## ክልሉ ለባለሀብት ሲተላለፍ የሚችል 69 ሺህ ሄክታር መሬት አዘጋጅቷል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ግብርና እና ቱሪዝምን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት ላላቸው ባለሀብቶች ሊተላለፍ የሚችል 69 ሺህ ሄክታር መሬት ማዘጋጀቱን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስታወቀ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መሬትና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ አቶ አመንቴ ጌሺ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ያለበት፤ በርካታ የማዕድን ሃብት መገኛ፣ የውሃ ክምችት ያለው፣ የዓባይ ግድብ ግንባታ የሚካሄድበት አካባቢ እንደመሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጭ በጣም ሰፊ ነው።

ባለሃብቶች በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሊሰማሩባቸው የሚችሉባቸው በርካታ አማራጮች አሏቸው ያሉት ኃላፊው፤ በማዕድን ሃብት፣ በድንጋይ ከሰል፣ በወርቅ፣ በእምነ በረድ፣ በግራናይት፣ የዕጣን ምርት፣ የሆልቲካልቸር ልማት ዕድል መኖሩን አመላክተዋል።

የዓባይ ግድብ ግንባታን ተከትሎ በሚፈጠሩ የመስኖ ልማት፣ የዓሣ እርባታ፣ ቱሪዝም ዘርፍ፣ በሆቴሎች ዘርፍ፣ የእርሻ ስራ ላይ ሃብታቸውን ቢያፈሱ እንደሚጠቀሙ ጠቁመው፤ ምቹ የአየር ንብረት መኖሩ በተለይም አካባቢው ዘጠኝ ወራት ዝናብ የሚያገኝ፣ መሬቱ ለምና ሰፋፊ ያልለሙ የእርሻ መሬቶች መገኛ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አቶ አመንቴ ገለፃ፤ በእርሻ ኢንቨስትመንት በኩል መሬት ወስደው፣ ገንዘብ ተበድረው የጠፉ፣ የማያለሙ በርካታ ባለሃብቶች ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ የክልሉ መንግስት ጠንካራ ሪፎርም የወሰደው በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ ነው። በተለይም በመሬት በኩል ጠበቅ ያለ ርምጃ ተወስዶ የነበረው ብልሽት ተስተካክሏል።

በተወሰደው ሪፎርም ማልማት የማይችሉት ተነጥቀው ለማልማት አቅም ላላቸው አካላት በውድድርም በምደባም ተላልፎ ማልማት መጀመሩን በመጥቀስ፤ በክልሉ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሃብቶች ሊተላለፍ የሚችል 69 ሺህ ሄክታር መሬትም ተዘጋጅቷል ብለዋል።

በርካታ ኢንቨስተሮች በተለይ በእርሻ ስራ ተሰማርተው የሚያለሙበት አካባቢ መሆኑን የጠቆሙት የቢሮ ኃላፊው፤ ከጸጥታ እና ተያያዥ ችግሮች ጋር ተያይዞ ተቀዛቅዞ የነበረው ኢንቨስትመንት እያገገመ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ቢሮክራሲው በሚፈለገው ደረጃ አመርቂ ነው ብሎ በድፍረት ለመናገር ባይቻልም በተደረገው ማሻሻያ ለውጦች ታይተዋል። በአሰራር ስርዓት በኩል የቢሮክራሲ ማነቆዎች እየተሻሻለ ይገኛል።

የዓባይ ግድብ ግንባታ ሲጠናቀቅ አካባቢው የኢኮኖሚ ኮርደር ይሆናል። የኢትዮጵያ የልብ ትርታ ማዕከል የሚሆነው ቤኒሻንጉል ነው። ከፍተኛ መነቃቃት አለ። በአካባቢው የሚገኙ ከተሞችም እየለሙ ይገኛሉ ሲሉም ተናግረዋል።

ግድቡ ብቻውን የሚያመጣው ምቹ የኢኮኖሚ ሁኔታ ከግምት በላይ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ግንባታው በመጠናቀቅ ላይ እንደመሆኑ በቅርቡ በርካታ ዓይነት የስራ እድሎች ይፈጠራሉ፤ በመሆኑም ቤኒሻንጉልን ለማልማት ወስኖ ወደ አካባቢው ለሚገባ ባለሃብት በቀጣይ ትልቅ ዕድል አለው ብለዋል።

ኃላፊ እንዳሉት፤ በክልሉ ፓርክ ይገነባል። ለዚህም የቦታ ርክክብ ተደርጓል፣ የግንባታ ስራውም ጅምር ላይ ነው፣ ሁለት ዓመታት ጊዜ የግንባታ ስራው ተጠናቅቆ ወደትግበራ እንደሚገባ ኃላፊነት የወሰደው አካል አሳውቋል።

የአካባቢው የጸጥታ ሁኔታ ልማቱ ላይ ተጽዕኖ አሳድሮ ነበር። አሁን የጸጥታው ችግር በመወገዱ የሚያሰጋ ነገር የለም፤ ዝርፊያ ግድያ ሙሉ ለሙሉ ቆሟል። ችግሩን መቆጣጠር በመቻሉ በቀጣይ የሚገባው ወደ ልማት ነው። ታጣቂዎች ትጥቃቸውን ፈትተው ገብተው ወደ ኢንቨስትመንት፣ ወደ እርሻ ስራ እየተሰማሩ ይገኛሉ ሲሉም ተናግረዋል።

# ዞኑ 24 ሚሊዮን የቡና ችግኞችን ለመትከል ቅድመ ዝግጅት እያደረገ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የቤንች ሸኮ ዞን በዘንድሮው ዓመት 24 ሚሊዮን የቡና ችግኞችን ለመትከል የሚያስችለውን ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

የቤንች ሸኮ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ጉብላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለ ምልልስ፤ ዞኑ በመጪው ክረምት 24 ሚሊዮን የቡና ችግኝ ለመትከል አቅዶ እየሠራ ነው ብለዋል። በዚህ መሰረትም የቡና ማሳ ልየታ፣ የጉድጓድ ዝግጅት፣ ችካል መቸከልና ሌሎች ለቡና ተከላ የሚስፈልጉ ግብአቶች እያሟሉ መሆኑን ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ቡና ከሚያመርቱ አካባቢዎች መካከል የቤንች ሸኮ ዞን አንዱ መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ ዞኑ የክልሉን 50 በመቶና የሀገሪቱን 10 በመቶ የሚሆን የቡና ምርት ያቀርባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት ለዓለም አቀፍ ገበያ ካቀረበችው 300 ሺህ ቶን የሚሆን ቡና ውስጥም የቤንች ሸኮ ዞን 30 ሺህ 400 ቶን ቡና ማቅረብ ችሎ እንደነበር በአስረጂነት አንስተው፤ በተያዘው ዓመት ዞኑ 308 ሺህ 850 ኩንታል ለማቅረብ አቅዶ እስከ አሁን ድረስም 171 ሺህ ኩንታል ቡና ለዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ ችሏል



አቶ መስፍን ጉብላ

ብለዋል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ አሁን ባለው ሁኔታ በገበያው አለመረጋጋት አርሶ አደሩ በቂ ቡና እያወጣ ባለመሆኑ የቀረበው ምርት ከታቀደው አንጻር አነስተኛ ቢሆንም በቂ ክምችት በመኖሩ ዞኑ እቅዱን ማሳካት ይችላል።

በዞኑ 220 ሺህ የሚሆኑ አርሶ አደሮች በቡና ማምረት ላይ የተሰማሩ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ አምና በቡና ምርት የተሻለ ገበያ በመኖሩ የተነሳም በርካታ አርሶ አደሮች በዚህ ዘርፍ ተሰማርተው ጥራቱን የጠበቀ ቡና እያቀረቡ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል። በተያዘው ዓመት ሚያዝያ ወር የቀረበው ምርት ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ60 ሺህ ኩንታል ብልጫ ያለው ምርት ለማእከላዊ ገበያ ማቅረብ መቻሉን እንደማሳያ አንስተዋል።

በቤንች ሸኮ ዞን ከቡና ምርት በተጨማሪ እንደ ኮረሪማ፣ ቁንዶ በርበሬ፣ ዝንጅብል፣ እርድና ጥምዝ የቅመማ ቅመም ምርት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚመረት የጠቀሱት ኃላፊው፤ በቅመማ ቅመም ምርቶች 127 ሺህ ቶን የሚሆን ምርት ለማምረት ታቅዶ እስከሁን ድረስ ስድስት ሺህ 500 ቶን ለማእከላዊ ገበያ ቀርቧል። በተለይም የእርድና የዝንጅብል ምርቶች በባለሀብቶች እየተመረቱ ለውጭ ገበያ እየቀረቡ ይገኛሉ።

የኮረሪማ ምርትን በተመለከተም በስፋት እያንዳንዱ አርሶ አደር እያመረተ ሲሆን፤ በተጨማሪም 11 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ ማሳ እየለማ ነው። በዞኑ ትላልቅ በሆኑት ደቡብ ቤንች፣ ሰሜን ቤንችና ጉራፈርዳ ወረዳዎች በስፋት ቅመማ ቅመም እየተመረተ ሲሆን፤ በዚህ ዘርፍ ላይም 96 ሺህ 500 የሚሆኑ አርሶ አደሮች ተሰማርተዋል።

# የመምህራን ምክክር የጋራ አስተሳሰብን ለማዳበርና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በየደረጃው የተካሄዱ ምክክሮች ከመምህራን ጋር የነበሩ የአስተሳሰብ ልዩነቶችን በማቀራረብ አንድነትን ያጠናከረ እና ለቀጣይም መነሳሳትን በመፍጠር የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ 60 ሺህ 587 የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት መምህራን ተቀላቅለው በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ለሁለት ቀናት በአገራዊ፣ በከተማና በትምህርት ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሂደዋል።

በሦስት ዙር በተካሄዱ የመምህራን የውይይት መድረኮቹ የሰላምና ደህንነት ሁኔታ፣ የመኖሪያ ቤት ጥያቄ፣ የደመወዝና ጥቅማ ጥቅምና ኑሮ ውድነት ትኩረት እንዲሰጠው በመምህራን ተነስቷል ብለዋል።

ምክክሩ በቀጣይ የጋራ አስተሳሰብ በመፍጠር እና የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን በተደራጀ አግባብ ለማስቀጠል የጎላ ሚና እንዳለውም የጠቀሱት አቶ ሲሳይ፤ የተገኙ ስኬትና ትሩፋቶች እንዲሁም ያጋጠሙ ፈተናዎች ላይ ውይይት መደረጉንም አስታውሰዋል።

ከመምህራን ጋር በወረዳዎች፣ በክፍለ ከተሞችና በከተማ ደረጃ ማጠቃለያ መድረክ መካሄዱን ያስታውሱት ኃላፊው፤ በለውጡ ሂደት ከመምህራንና ከማሕበረሰቡ ጋር የጋራ መግባባት ለመፍጠር ይዞ የተነሳውን ዓላማ ማሳካት ችሏልም ነው ያሉት።

ውይይቱ የግልና የመንግስት መምህራን በሚል ይነሳ የነበረውን ክፍፍል በማቀራረብ አንድነትና ወንድማማችነትን ለማጠናከር እንዳስቻለም ጠቁመዋል።

ለውጡን የማይፈልጉ አካላት ውይይቱን ለማደናቀፍ ሙከራ ሲያደርጉ እንደነበርና በርካታ ጉዳዮች ተነስተው መግባባት ላይ መደረሱንም ነው የጠቆሙት። በተለያዩ ክልሎች የዜጎች መፈናቀልና ሞት እንደነበር፣ እነዚህን



አቶ ሲሳይ እንዳለ

ጉዳዮችም ወደ ከተማ አስተዳደሩ ለማምጣት ጫናዎች መታየታቸውንና ችግሮቹንም ወደ ትምህርት ቤት ለማስጠጋት ሙከራዎች መደረጋቸውን በውይይቱ ወቅት ተነስቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ሲሳይ ገለጻ፤ ምሁራን የመማር ማስተማር ሂደቱ ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል የጎላ ሚና ነበራቸው፤ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ መግባባት ላይ ተደርሷል። ከዚህ በፊት ለመምህራን በኪራይ ተሰጥቷቸው የነበሩ አምስት ሺህ የሚጠጉ ቤቶች ወደ ግላቸው እንዲዞር የተደረገውን ውሳኔ እንዲሁም 800 ብር የነበረው የድጎማ አበል ወደ ሶስት ሺህ ብር እንዲያድግ መንግስት እያደረጋቸው ያሉ ውሳኔዎችንም አድንቀዋል።

መምህራን ከኑሮ ውድነት አኳያ የሚከፈላቸው ደመወዝ በቂ ባለመሆኑ መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት መነሳቱን፣ የመኖሪያ ቤት ለመምህራን መኖሪያ ብቻ ሳይሆን መስሪያ ቦታ ጭምር እንደመሆኑ በዚህ መነሻ የመኖሪያ ቤት ጥያቄን ለመፍታት መንግስት እያደረገ ያለው ጥረት ሊፈጥን የሚገባ መሆኑ በመምህራን ተነስቷል። ለመደራጀት ቁጠባ መጀመር እንደሚገባቸውም በመድረኮቹ ተነስተው የጋራ መግባባት ተደርሷል።

ከኑሮ ውድነት አንጻር መምህራን አገራዊና ከተማዊ ነባራዊ ሁኔታን እንዲገነዘቡ መደረጉን፣ በቀጣይም መንግስት እየሰራ ያለውን ስራ እንዲገነዘቡ እና የድርሻቸውንም እንዲወጡ መግባባት መደረሱን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ትምህርት ቤቶች ከመማር ማስተማሩ ጎን ለጎን የእርሻ ቦታዎች ለማድረግ መስራት እንዳለበት መነሳቱንና መግባባት ላይ መደረሱንም ጠቁመዋል።

በትምህርት ቤቶች አካባቢ ተነስቶ የነበረው አዝማሚያ ትክክል እንዳልነበረ፣ ከመማር ማስተማር ስራ ውጪ የሚታዩ ዝንባሌዎች ትክክል ባለመሆናቸው መታረም እንዳለባቸው መግባባት ላይ መደረሱንም አቶ ሲሳይ አመልክተዋል።

# የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በፖሊሲና በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘላቂነት ይቀጥላል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስአበባ፡- በቀጣይ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በፖሊሲና በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘላቂነት ለማስቀጠል እንደሚሰራ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄና ውጤቶቹን የሚያስቃኝ የፓናል ውይይት በሚሊኒየም አዳራሽ በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በመድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ በቀጣይ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄን በፖሊሲና በቴክኖሎጂ በመደገፍ በዘላቂነት ለማስቀጠል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በትኩረት ይሰራል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ ንቅናቄው ማምረት ያቆሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት እንዲገቡ ያስቻለ ሲሆን፤ በዚህም ከ352 በላይ ኢንዱስትሪዎች ወደ ምርት እንዲገቡ ለማድረግ ተችሏል።

የአገራት ማንነት በሚያመርቷቸው የምርት መጠንና አይነቶች እንዲሁም በቴክኖሎጂ የሚወሰን ነው ያሉት አቶ መላኩ፤ በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለኢትዮጵያ የችግር መውጫ በር ነው ሲሉ ገልፀዋል።

አቶ መላኩ እንደገለጹት፤ ማምረት ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ነው፤ እንደ አገር ያለውን ሰፊ ሀብት በማምረት መጠቀም ይገባል።

አንድነትና ህብረትን በመፍጠር የአምራች ኢንዱስትሪውን ባህል ማሳደግ እንደሚገባም ገልፀዋል።

በንቅናቄው በዘርፉ የነበረውን የቅንጅት ችግር ለመቅረፍ ጥረት ተደርጓል። በዚህም በፌዴራልና በክልሎች መካከል በተሰራ ሥራ መሻሻሎች አሉ ሲሉም ገልፀዋል።

በሌላ በኩል በዘርፉ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰው፤ በማህበረሰቡ፣ በአመራሩና በአምራቾች ላይ ውጤታማ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል።

በተጨማሪም የመሬት አቅርቦት፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ጨምሮ ከውጪ አገር የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በመተካት መሻሻሎች መታየታቸውን አመልክተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም አካል ነው ብለዋል።

የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግና ለአምራች ኢንዱስትሪ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል ሥራ በመሰራት ላይ መሆኑንም አቶ አህመድ ገልጸዋል።

መንግሥት በግሉ ዘርፍ የኢንዱስትሪን ሚና ለማሳደግ የሚያስችል የፋይናንስ አቅርቦትን አጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉም ጠቁመዋል።

የተለያዩ አገራዊና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች በውጭ ምንዛሪው ላይ ጫና ማምጣታቸውን የጠቀሱት አቶ አህመድ፤ መንግሥት ጫናውን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን ገልፀዋል።

ውይይቱ የፕላንና ልማት ሚኒስትር በዶክተር ፍጹም አሰፋ የተመራ ሲሆን፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ፣ የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታን ጨምሮ የፌዴራል ከፍተኛ ኃላፊዎችና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል።

# "የግብርና ምርታማነትን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እና የሁለንተናዊ ለውጥ አጀንዳዎች የጀርባ አጥንት ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ግብርናውን ማዘመንና ከተለመደው አሰራር በመውጣት አዲስ አተያይ መተግበር የግብርና ምርታማነት ለመጨመር የሚያስፈልግና ትኩረት የሚሻ መሆኑን ገልጸዋል።

ለአብነትም የቆላ ስንዴ ከተለመደው አስተሳሰብ ወጣ ተብሎ የተተገበረ በመሆኑ ዛሬ ትልቅ ውጤት አግኝተንበታል። ከስንዴ የተገኘውን ውጤታማ ጉዞ ትምህርት በመውሰድም በሩዝ፣በበቆሎ፣ በቡና፣ በሌሎች ሰብሎችና ፍራፍሬዎች በምርታማነት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት አዲስ ዕይታ ያስፈልጋል ብለዋል።

የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ በምግብ ራስን ከመቻልና በራስ ከመኩራት ጉዳይም ጋር የሚያያዝ ጭምር መሆኑን ጠቁመው፤ ግብርና የተፈላጊነቱን ያህል ትኩረት ልንሰጠው ይገባል ብለዋል።

ስለ ግብርና ስንመክር በሌሎች መስኮችም ያለውን ተጽዕኖ አብሮ ማሰብ እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ምርታማነትን ለመጨመር ግብርናን ማዘመንና ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን ስራ ላይ ማዋል እጅግ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል። ግብርናውን ከስነ ምግብና ከግብይት ስርዓቱ ጋር በማስተሳሰር መስራት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

በአሁኑ ጊዜ እንደ ከዚህ በፊቱ የዝናብ ወቅትን ብቻ እየጠበቁ ግብርናን ማስኬድ አይቻልም ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፤ ግብርናውን በሜካናይዜሽን እና በሌሎችም ቴክኖሎጂዎች መደገፍ ያስፈልጋል ብለዋል። ይህም የአሁኑ ትውልድ የቤት ስራ ነው ብለዋል።

በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተው የግብርና ምርታማነትን የሚያሳድጉ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ እና የምርምር ፈጠራዎች ዐውደ ርዕይ ላይ የቀረቡ የቴክኖሎጂና የምርምር ውጤቶች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውንም ገልጸዋል።

የግብርና ሚኒስትሩ ግርማ አመንቴ(ዶክተር) በበኩላቸው ቀደም ሲል የግብርናን ምርታማነት ከማሳደግና ከማዘመን አኳያ ውስንነቶች እንደነበሩ አስታውሰው፤በአገራዊ ለውጡ ማግስት ጀምሮ ግብርናውን ለማዘመንና ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቷቸው በተሰሩ ስራዎችም ውጤቶች መገኘታቸውን ተናግረዋል።

ለአብነትም ግብርናውን ለማዘመን ከ500 በላይ ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ መደረጉን፤ አርሶ አደሩ ከፋይናንስ ተቋማት በብድር የሚያገኝበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን፤ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ ለማዳበሪያ 36 ቢሊዮን ብር ድጎማ መደረጉን ጠቅሰዋል።

የፓናል ውይይቱ በስንዴ ልማት የተገኘውን ስኬት በሌሎች ምርቶች ለመድገም ተሞክሮ የሚወሰድበት፣ ግብርናውን በቴክኖሎጂ ለማዘመን የሚያስችሉ አሻጋሪ ሃሳቦች የሚንፀባረቁበት እና ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚቀመጡበት እንደሆነም ተጠቁሟል።

# "ትውልዱ የሚያነብ፣ ነገሮችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**



በመርሀ ግብሩ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) እንደተናገሩት፤ የመጭዋን ኢትዮጵያ መፃኢ እድል ከሚወስነው ትውልድ ጋር መወያየትና ሀሳብ መቀበል ጠቃሚ ነው። ትውልዱ የእኔ ይበልጣል ከሚል እሳቤ በመውጣት በመከባበርና በመቻቻል ሁሉንም ነገር በቀና አመለካከት በማየት አዲሲቷን ኢትዮጵያን እውን የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

አክለውም ለሀገር ተረካቢው ትውልድ "ኢትዮጵያ የእናንተ ናት፤ እኛ አሁን ከእናንተ በመዋስ አሳምረንና አስውበን ለእናንተ የምናስረክባት ሀገር ላይ ነው ያለነው" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ቀደም የነበረው እሳቤ "ከአባቶቻችን የወረስናት" የሚል እሳቤ ነው ብለዋል።

በንግግራቸውም "ኢትዮጵያ ላይ እኛ መሠረት ነው የምንጥለው፤ እናንተ ደግሞ በተሻለ መልኩ አሳምራችሁ ለቀጣይ ትውልድ መስራት ይጠበቅባችኋል" ብለዋል።

ኢትዮጵያን ካለፈው ትውልድ የተረከብናት ብቻ ሳትሆን ከልጆቻችን የተዋስናት ጭምር በመሆኗ ሁላችንም የተሻለ ነገን በሚመጥን አግባብ ልንገነባት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

አካላቶቻችን በአንድ ላይ ተሰናስለውና ተደምረው ሲሰሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ በመረዳት ትውልዱ በአንድነት ሊሰራ ይገባል ነው ያሉት።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም ትውልዱ ችግር ላይ ማተኮር ሳይሆን የመፍትሔው አካል መሆን እንዳለበትም ተናግረው፤ መደመር ስንል አንድ ግለሰብ ከሌላው ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሱ ጋርም የሚስማማበትን ሃሳብ የያዘ ነው ብለዋል።

የመደመር ትውልድ አካል የሆኑት ወጣቶቹ የመደመር መጻሕፍት በሰላምና በኢትዮጵያዊነት የሚያምን ትውልድን የሚቀርፅ ነው፤ እኛ የምንረከባት የነገይቱ ኢትዮጵያ በዕውቀት የተገነባች ጠንካራ አገር እንደምትሆን በመጽሐፉ ላይ በሚገባ ተጠቅሷል ብለዋል።

መጽሐፉ መተባበርና አብሮነትን በልዩነት እንደሚያነሳ ያብራሩት ወጣቶቹ፤ ኢትዮጵያዊነትን ከአፍሪካዊነት እንዲሁም ከዓለም አቀፋዊነት ጋር አዋህዶ እንደሚያብራራ ተረድተናል ብለዋል።

የመደመር ትውልድ ኢትዮጵያን ለመገንባት ትልቅ ኃላፊነት አለበት ያሉት ወጣቶቹ፤ ትውልዱ በእውቀት ዳብሮ ተሻጋሪ መሆን እንዲችል እንደ አብርሆትና ሳይንስ ሙዚየምን የመሳሰሉ ዘመን ተሻጋሪና የትውልድ መቅረጫ ተቋማት ማሳያ ናቸው ሲሉ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት ችግር የብሔር አክራሪነት ዋነኛ መንስዔ ነው ያሉት ወጣቶቹ፤ ትውልዱ ከዚህ ችግር መውጣት እንዳለበት ተናግረዋል።

የአንድ ሀገር መነሻ ታሪክና ባህል መሆኑን በመጥቀስም፤ ትውልዱ የተሻሉ እሳቤዎችን ከታሪክ በመማር ሀገሩን ለመቀየር ትኩረት ማድረግ እንዳለበት በማመን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ትውልዱን የሚቀርፅ እንዲህ ያለ መፍትሔ እና አቅጣጫ ጠቋሚ መጽሐፍ ስላበረከቱልን እናመሰግናለን ብለዋል።

አክለውም በሀገር በቀል እውቀቶች የዳበረ ምቹ የትምህርት ሥርዓት እና ከባቢ እንዲፈጠርላቸውም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ባህል እና ታሪክን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የሚያምን እና የሚታመን፣ በሥነ ምግባር የታነፀ ትውልድን ለመፍጠር እየተሰሩ ያሉ አበረታች ስራዎችንም ተማሪዎቹ አንስተዋል።

የነገው ሀገር ተረካቢ ትውልድ መልካም ሥነምግባር ያለው እንዲሆን መንግስት ተጠያቂነትን ማስፈን አለበት፤ በተለይ የነገውን ትውልድ ለመገንባትና የዲሞክራሲ አረዳድ እንዲስፋፋ መሠረተ ልማቶች በየክልሎቹና በየገጠሩ መገንባት ይኖርባቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

በመጽሐፉ ላይ የመደመር ትውልድ ተብሎ የተገለጸው እነሱ የሚወክሉት ትውልድ የኢትዮጵያ ተስፋ መሆን እንዳለበት የገለጹት ተማሪዎቹ፤ አሁን ያለው ትውልድ ደግሞ ችግሮችን በውይይት በመቅረፍ የሚያምን፣ ጠንካራ የትምህርት ሥርዓትን በመፍጠር የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማሻገር የሚጥር እንዲሆን መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የማጠቃለያ መርሀ ግብሩ በመጪው ትውልድ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን፤ የመደመር ትውልድ መጽሐፍን ያነበቡ ተማሪዎች በመጽሐፉ ዙሪያ የተለያዩ ሃሳቦችን በመስጠትና ከመጽሐፉ ውስጥ የመረጡትን አርዕስት በመምረጥ ሃሳባቸውን አንፀባርቀዋል። ለጠቅላይ ሚኒስትሩም ምስጋናና መልዕክታቸውን አቅርበዋል።

"ቃል፤ ተግባር፤ ትውልድ" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚያዝያ 24 እስከ 29/2015 ዓ.ም የቆየው ዐውደ ርዕይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአመራርነት ዘመናቸው ለህዝብ ያቀረቧቸው የህትመት ውጤቶች የተዋወቁበት፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ባለፉት ዓመታት የተፃፉ ሥራዎች የተገመገሙበት እና የመጽሐፍ ሽያጮች የተከናወኑበት እንዲሁም የንባብ ባህልን ለማሳደግ የሚያግዙ ውይይቶች የተካሄዱበት ሆኖ በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል።

# ግብርናውን ለማዘመንና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

እየታዩ ነው። እነዚህን ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማስፋት ይገባል።

ኢትዮጵያ በስንዴ፣ በማር ፣በቡና፣በእንስሳትና በሌሎች ምርቶች በአፍሪካ ግንባር ቀደም ብትሆንም እነዚህ የግብርና ምርቶች ለዓለም ገበያ ቀርበው ገንዘብ አምጥተው ችግራችንን የሚፈቱበት ደረጃ ግን አልተሻገሩም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ግብርናን ለማዘመንና ምርታማነትን ለማሳደግ በእንስሳት ፣በማር፣ በቡና፣በስንዴና በሌሎች ምርቶችም እየተሰሩ ያሉትን ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ማስፋት እንደሚገባም ገልጸዋል።

ከዛሬ 30 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ህዝብ ከ50 ሚሊዮን እንደማይበልጥ ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በፍጥነት እያደገ ለመጣው የህዝብ ቁጥር የሚፈልገውን ምግብ ለማሟላትና ለውጭ ገበያ አቅርቦት የሚፈለገውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ግብርናውን ማዘመን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

የግብርና ምርትና ምርታማነትን በሁሉም ዘርፍ በመጨመር የምግብ ዋስትናን ከመሸፈን ባለፈ ለውጭ ገበያ ማቅረብና አስተማማኝ ኢንዱስትሪ ግብዓት በቀላሉ ማግኘት እንደሚቻል ያብራሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በግብርና ምርትና ምርታማነት ላይ ማነቆ የሆኑትን የአፈር ለምነትና ሌሎች ችግሮችን ሳይንሳዊ መንገድ በመከተል መፍታት ይኖርብናል ብለዋል።

የኢትዮጵያን ልማት ለማሳደግ በቀዳሚነት በግብርናው ዘርፍ ሰፊ ሥራዎች ሲሰሩ እንደቆዩ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ዕውቀትን ለማዳበር፣ ፈጠራን ለማነሳሳት እና የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንቶችን ለማበረታታት የተሰሩ ስራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባም ገልጸዋል።

የግብርና ምርቶችን በብዛትና በጥራት ለማምረት ግብርናው በቴክኖሎጂ መዘመን እንደሚገባው አመልክተው፤ አውደ ርዕዩ ግብርና ከተለያዩ ሳይንስና ቴክኖሎጂዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳየና የግብርና ሳይንሳዊ አጠቃቀምና አተገባበር ላይ ትምህርት የሚገኝበት ነው ብለዋል።

የሳይንስና የግብርና አውደ ርዕዩም ተማራማሪዎች፣ በዘርፉ የሚሰማሩ አካላትና ባለሙያዎች ግብርናን እንዴት ምርታማ ማድረግ እንደሚችሉ ተሞክሮዎች የሚቀስሙበት እንደሚሆን አመልክተዋል።

እስካሁን የተሄደበትንና አሁን ያለንበትን የግብርና ቴክኖሎጂ አቅም የሚያሳይ አውደ ርዕይ በመዘጋጀቱም መደሰታቸውን ገልጸዋል።

ግብርና አሁን ያለበትን ደረጃና የቀጣይ ጉዞውን በተመለከተም ተማሪዎች፣ ወጣቶች፣ ተመራማሪዎችና ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት በሳይንስ ሙዚየም በመገኘት የግብርና ሳይንስ አውደ ርዕዩን እንዲመለከቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በግብርናና ሳይንስ አውደ ርዕዩ የእርሻ ትራክተሮች ፣ዘመናዊ የመውቂያ መሳሪያዎች፣ኮምባይነሮች፣ ዘመናዊ የንብ ማነቢያ ቀፎዎች፣ የተለያዩ ዘመናዊ የግብርና መሳሪያዎችና የተለያዩ የግብርና ምርምር ውጤቶች ለዕይታ ቀርበውበታል።

አውደ ርዕዩ በግብርና የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመለዋወጥ መልካም ዕድል የሚፈጥርና ለአንድ ወር የሚቆይ ሲሆን፤ እንደ አስፈላጊነቱ ሊራዘም እንደሚችል ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትምህርት ትውልድ የመቅረጽ ሚናውን እንዲወጣ!

ኢትዮጵያውያን በረዥሙ የሥርዓተ መንግሥት ግንባታ ጉዟቸው፤ ከፍ ያለ የጥበብና የእውቀት ባለቤት ስለመሆናቸው የሚያሳዩ አያሌ አሻራዎች አሉ። የሥነ ሕንፃ፣ የኪነ ጥበብ፣ የቅረጻቅርጽ፣ የሥነ ጽሑፍ፣ የፍልስፍና፣ የስነፈለግ፣... ጥበብ ባለቤት ስለመሆናቸው ብዙ ማመሳከሪያዎች ዘመን ተሻግረው ዛሬም ሕያው ሆነው ይታያሉ። ሌላው ቀርቶ የራሳቸውን ፊደል ቀርጸው፣ የራሳቸውን ዘመን ቀምረው ከሚጠቀሙ ጥቂት የዓለም ሕዝቦች ውስጥ ከቀዳሚዎቹ ተርታ መሆናቸው ግልጽ ነው።

ይሄን እውቀት ግን ዝም ብለው ከፈጣሪ በተሰጣቸው ጸጋ ብቻ ያገኙት አይደለም። ይልቁንም በኢ. መደበኛ የትምህርት ሥርዓት (በዋናነት በየቤተ እምነቶች፣ ከፊደል ቆጠራ እስከ ፈጠራ በሚገለጽ መልኩ) በሚሰጡ ትምህርቶች እንጂ። ለዚህም ብራና ፍቀው፣ ቀለም በጥብጠው የከተቧቸው የጥበብ ውጤቶቻቸው ምስክር ይሆናሉ። በዘመናት ጅረት ውስጥ ታዲያ ይሄ ኢ.መደበኛ የትምህርት ሥርዓት በመደበኛ የትምህርት ሥርዓት እየተተካ ሄደ። ትምህርት ከቤተ እምነቶች ወደ ዓለማዊው ትምህርት ቤት ተሸጋገረ።

ይሄ መልካም የሚባል አገራዊውንም፣ ዓለምአቀፋዊውንም እውቀት መገብየትን፤ በዚህም ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ጥበብ ከሌሎች ጋር አዋህደውና አናብበው ከፍ ያሉ ሥራዎችን እንዲሠሩ ዕድል የፈጠረም ነበር። ይሁን እንጂ በሂደት የትምህርት ሥርዓቱ ከአገራዊ እሴቱ እየተፋታ የውጭው ፍልስፍናና አመለካከት ላይ እየተንጠለጠለ ሄደ። ትውልድንም አገርንም ዘመን አሻግሮ ከፍ ላለ ክብር ያበቃው አገራዊው እውቀት ኋላ ቀር ተብሎ፤ ከውጭ የተገለበጠው እሳቤ በዘመናዊነት ተንቆለጳጵሶ የትምህርት አውዱን ዙፋን ተቆናጠጠ።

ሆኖም ዓሣ ከባህሩ ከወጣ ሕይወቱ እንደማይቀጥል ሁሉ፤ የኢትዮጵያም የትምህርት ሥርዓት ከባህሉ በተፋታ ቁጥር አገራዊ ፋይዳው እየወረደ፤ የእውቀትና የፈጠራ መድረክነቱ እየነጠፈ፤ በአንጻሩ የውጭው አስተሳሰብ ጥገኛ እየሆነ ሄደ። ይሄም ትውልዱ ከመፍጠር ይልቅ መኮረጅ ላይ እንዲያተኩር ብቻ ሳይሆን፤ ከክፍል ክፍል የሚደረጉ ሽግግሮችን ሳይቀር በፈተና ኩረጃ ላይ እንዲንጠለጠል አደረገው። ይሄን የኩረጃ መንፈስ ከፍ ያደረገው ደግሞ በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ተዋናዮች ጭምር ችግሩን አይቶ እንዳላየ ማለፍ ነበር።

ይህ የትምህርት ሥርዓቱ በዚህ ደረጃ ከራስ እውቀትና እሴት መፋታት የፈጠረው አጠቃላይ የትምህርት ውድቀት ታዲያ፤ ትውልድን ብቻ ሳይሆን አገርንም ከፍ ያለ ዋጋ አስከፍሏል። የዚህ ትልቁ ማረጋገጫ የሆነው ደግሞ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ብሔራዊ ፈተና እንደ አገር በተለየ መልኩ በየዩኒቨርሲቲዎች እንዲሰጥ መደረጉ ነበር። ምክንያቱም በዚህ ፈተና ኩረጃ እንዳይካሄድ በመደረጉ ብቻ ከተፈተኑ አጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ ሦስት በመቶ ያህሉ ብቻ የፈተናውን ሃምሳ በመቶ መመለስ መቻላቸው ነው።

ይሄ ደግሞ እንደ አገር ያለው የትምህርት ሥርዓት ምን ያህል የታመመ እንደሆነ በግልጽ ያረጋገጠ ሲሆን፤ ችግሩን ቀደም ብሎ መለየት የተቻለ ቢሆንም በዚህ ልክ ተገንዝቦ ለመፍትሄው ያልተሠራ እንደመሆኑ በቀጣይ ለችግሩ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲሠራበት ያደረገ ነበር።

ለዚህ ሥራ መልካም አጋጣሚ የሚፈጥረው ደግሞ፣ ከአገራዊ እሴቶችና እውቀቶች የተፋታው የትምህርት ሥርዓት በአገራዊ እሴቶችና እውቀቶች ቅኝት እንዲታገዝ የሚያስችል፤ ለተማሪዎች ክህሎትና ሥነምግባር ትኩረት የሚሰጥ፤ የባለድርሻዎችን ብርቱ ድጋፍና ተሳትፎ የሚያሳድግ፤ የተማሪዎችን የመመራመርና የመፍጠር አድማስን የሚያሰፋ፤... የትምህርት ፖሊሲ መቀረጹ ነው። ይሄን ውጤታማ ለማድረግም በትምህርት ቤቶች፣ በመምህራን፣ በትምህርት ግብዓቶች እና በራሱ በመማር ማስተማርና ምዘና ሥርዓቱ ላይ እየተወሰዱ ያሉ አበረታች ርምጃዎች መኖራቸውም የሚበረታታ ነው።

የእነዚህ ድምር ውጤት በጠንካራ የዘርፉ አሠራርና አመራር ተደግፎ መሄድ ከቻለ፤ የትምህርት ሥርዓቱን ስብራት መጠገን ብቻ ሳይሆን የተሻለ አገራዊ አቅም ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ይሄን የሚሸከም የመፍጠርና የማሰላሰል አቅም ያለው ትውልድ ማፍራት ያስችላል። በመሆኑም ትምህርት ትውልድን በእውቀት እና በሥነምግባር የመቅረጽ ሚናውን እንዲወጣ የማድረግ ጅምር ሥራዎች ሊጎለብቱ፤ ለዚህም ሁሉም ባለድርሻ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሱሰኝነትን የመዋጋቱ ቁርጠኝነት

ሰላማዊት ውቤ

በኢትዮጵያ ከቅርብ አመታት ወዲህ በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ እና በትላልቅ ከተሞች የጫትና የአደገኛ አደንዛዥ ዕጽ ዝውውርና ተጠቃሚነት በእጅጉ ጨምሯል። በቤት ውስጥ በጎጆ ኢንዱስትሪ ከሚመረት ጠላና አረቄ ጀምሮ በፋብሪካ እስከ የሚመረቱ ቢራና ሌሎች የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች ምርት ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይስተዋልም።

ቢራን ብቻ ብንወስድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ባልደረባ የሆኑት ፕሮፌሰር ሰለሞን ተፈራ ሰሞኑን ይፋ ባደረጉት አንድ ጥናታቸው እንደጠቆሙት፣ እኤአ በ2000 በየዓመቱ 100 ሚሊዮን ሊትር አካባቢ ይመረት ነበረ ሲሆን በየዓመቱ ከ15 እስከ 20 በመቶ እያደገ አሁን ዓመታዊ ምርቱ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ሊትር ደርሷል። በአማካይ ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ 12 ሊትር ይደርሰዋል።

አምራች ፋብሪካዎቹም በእጅጉ ተስፋፍተዋል። ሁላችንም እንደምናስተውለውም ቢራ ሽቀጣ ሸቀጥ መደብሮች ሁሉ ገብቶ ይቸረቸራል። የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ፈቃድ ያላቸው እነዚህ መደብሮች ፈቃድ ባይኖራቸውም በይፋ ከመኪና ላይ ቢራ ያወርዳሉ።

ከ21 ዓመት በታች ላሉ ወጣቶች ማናቸውም የአልኮል ይዘት ያላቸውን መጠጦች መሸጥ በአገራችን ሕግ የተከለከለ ቢሆንም እነዚህ መደብሮችም ሆኑ ትላልቅ ቡና ቤቶችና ሌሎች ቢራን ከ21 ዓመት በታች ላሉ ይባስ ብሎም ለ12 እና ለ15 ዓመት ታዳጊዎች ሁሉ ሲሸጡ ይስተዋላል። ጠጅ እንዲሁ ያለ ዕድሜ ገደብ ገንዘብ ለከፈለና ለመጠጣት ለፈለገ ሁሉ ሲቸበቸብ ማየቱ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ጠላና አረቄ (ካቲካላ)ም እንዲሁ በቤት ውስጥ በጎጆ ኢንዱስትሪ በየሥርቻው ሳይቀር በስፋት እየተመረቱ ለመጠጥ በሽያጭ የሚቀርቡበት ሁኔታ አለ። የእነዚህም ተጠቃሚ ቁጥር ቀላል አይደለም።

እነዚህ መጠጦች በሚቸበቸቡባቸው ቤቶች በአብዛኛው በማስከር፤ ዱላ በማማዘዝ ሲያደባድቡ፤ ሲያጯጩሁና ሲያጋጩ በየአካባቢያችን የምናስተውለው ታዳጊውንና ወጣቱን የኅብረተሰብ ክፍል ነው።

ከእነዚሁ ጎን ለጎን በአገራችን በብዙ አካባቢዎች በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ፤ ሌሎች አካባቢዎች ጫት መቃሚያ ቤቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመሩ ናቸው። በለጬ፤ የአወዳይ፤ የባህር ዳር፤ የጅማ ጫት አለ እየተባለ በሚሸጥባቸው በእነዚህ ጫት ቤቶች ስንገረም በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ተቋምና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዙሪያ የሻይ ቡና እና የምግብ አገልግሎት ለመስጠት ነው የተቋቋምነው የሚሉት ቤቶች በድብቅ በየጓዳቸው ጎዝጉዘው የተማሪውን አእምሮ ሲያናውዙ ይስተዋል። :

ቢራና የአበሻ አረቄ (ካቲካላ)ም በዚያው ጓዳ ሲያቀርቡ ማስተዋሉ የተለመደ ነው። ይሄም ብቻ ሳይሆን በእነዚህ በትምህርቱ ተቋማት ዙሪያ ያሉ ቤቶች ውስጥም ጫት ብቻ ሳይሆን ኮኬን፤ ሄሮይንና ሌሎች አደገኛ ዕጾችም በስውር ይቀባበላሉ። ይዘዋወራሉ። ቶባኮ ያስጨሳሉ።

አብዛኛው በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖርም ሆነ የሚማርና የሚያድግ ታዳጊና ወጣት የኅብረተሰብ ክፍል የአደገኛ አደንዛዥ ዕፆች እና የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች የሱስ ተገዢ ለመሆን ተገድዷል። በቅርቡ ይፋ በሆነ አንድ ጥናት አሁን በአገራችን ካለው አጠቃላይ ወጣት 4 ነጥብ 4 በመቶ የሚሆነው በእነዚሁ የአደገኛ ዕፆችና የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች ሱስ የተፀናወተው መሆኑ ተረጋግጧል።

ጥናቱ በዚህ ምክንያትም በተለይ እነዚህ ቤቶች ባሉበት በሁለተኛ ደረጃና ከፍተኛ ትምህርት የሚማር ተማሪ በትምህርቱ ውጤታማ መሆን አለመቻሉን ጠቁሟል። ባህርይው መቀየሩና ባህላዊና ማህበራዊ እሴቱ መሸርሸሩ ተጠቅሷል። በአንዳንድ ሱሰኛ ወጣቶች ላይ እንደምናስተውለው ሱስ የሆነባቸውን ባጡ ጊዜ በጣም ይበሳጫሉ፤ ቁጡና በጥቂት ነገር የሚናደዱ ይሆናሉ።

ሱሳቸውን ለማርካት ወደ ስርቆት ከማምራት ባሻገር እስከ መደባደብና ሁከት መፍጠር፤ አስገድዶ እስከ መድፈርም ይደርሳሉ። ላልተፈለገ ተግባር የሚጋለጡበትም ጊዜ ብዙ ነው። ግለ ወሲብ ለመፈፀም ይገደዳሉ። በተለይ በፖርኖግራፊ ሱስ ተጠቂ የሆኑ ወጣቶች ብዙ ሰዓታትን በዚሁ ላይ ከማሳለፍ የተነሳ በአግባቡ ሥራቸውን ለማከናወን ይቸገራሉ። የእንቅልፍ መዛባትም ይገጥማቸዋል። የቤተሰብ፤ የማህበራዊና መንፈሳዊ ኃላፊነቶችን መወጣትም ይሳናቸዋል።

በአጠቃላይ በሱሰኝነቱ ምክንያት ወጣቱ የሥራ አቅሙ በእጅጉ ቀንሷል። የጤናው ሁኔታም ሲታይ በእጅጉ የተቃወሰ ለመሆን በቅቷል። ውጫዊ ማንነቱን (ፊዚካል ማንነቱ ወይም የፊቱ ገጽታ ቃሚና ጠጪ ሰካራም በመምሰል) ተቀይሯል። እየተገለለና ሰካራሙ፤ ቃሚው፤ ጠጪው በመባል በመጥፎ ስም እንዲጠራም ሆኗል። እንዲህ ዓይነቱ ወጣት ጭራሽ አገር ለመረከብም የሚታመን ዜጋ ሆኖ መገኘት የሚችልበት ሁኔታ ጠቧል።

ዕምቅ አቅማቸውን በመጠቀም በዕውቀት፤ በአመለካከትና በክህሎት ዳብረውና ስብዕናቸው ተገንብቶ ለአገር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ አዘቅዝቋል። በተለይ ባለፉት ዓመታት በሱሰኝነታቸው ሳቢያ በቀላሉ ለችግር በመጋለጥ ወደ ጥፋትና አፍራሽ ድርጊቶች የመግባት ዕድላቸው ሰፍቷል። ለልማትና ለሠላም ሊያውሉት የሚገባ ዕምቅ ኃይል፤ ዕውቀት፤ ጊዜና ገንዘብ በከንቱ እየባከነ ይገኛል። ይሄ ሁሉ በሱሰኝነታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው ያለ ችግር ነው።

ይሄንኑ የጥናት ግኝት ተከትሎም ጉዳዩ በበላይነት የሚመለከተው የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደ አገር ሱስ የተፀናወተው ከጽንውቱ እንዲያገግም፤ ያልገባውም ወደሱስ ጽንውተኝነት እንዳይገባ ለመታደግ እንደ አገር ለአንድ ዓመት የሚዘልቅ የንቅናቄ መድረክ ይፋ በማድረግ ጥሪውን ሲያቀርብ ተደምጧል።

በዚህ ከሚያዝያ 2015 እስከ ሚያዝያ 2016 ዓ.ም የሚዘልቅ መድረክ ወጣቶች ወደዚህ የአደንዛዥ ዕፅ ሱስ እንዳይገቡ የገቡትም በፍጥነት እንዲወጡ የተለያዩ የንቅናቄ ተግባራት እንደሚከናወኑም ታውቋል።

ይሄን ንቅናቄ በመተግበር ግቡን ከስኬት ለማድረስ በአገራችን አሁን ላይ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሁላችንም የምናውቀው ነው። ዛሬ በመላው ኢትዮጵያ እጅግ አስደሳች ሰላም ሰፍኗል። ከጦርነት ነጋሪት ፉከራ፤ ጥፋት ወጥተናል። ሰላም መልሶ ግንባታን የምንነጋገርበትን አጀንዳም አንስተናል።

ይህን የሰላም አየር ለማስቀጠልም በዚህ ሳምንትም የሁሉም ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች ወደ መቐለ አቅንተዋል። በብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ እየተመራ ወደ መቐለ የተጓዘው ልዑክ አላማም ያነቡ ዓይኖችን ለማበስ፤ የተበላሹ -የፈረሱ ቦታዎችን ለመጠገን ለክልሎች እንደ ወንድም ሕዝቦች ካላቸው ለማጋራትና ይሄን የሰላም ጅማሮ በተግባር ለማስቀጠል ነው።

ከኦነግ ሸኔ ጋር የሚደረገው ድርድር በታንዛንያ መጀመሩም ለዓመታት ሰላም ተጠምቶ ለመኖር የተገደደው ሕዝብ ትልቅ እፎይታ ነው። በዚህ ድርድር የሚሳተፉ ወገኖች ከግጭት፤ ከጦርነት ትርፍ እንደሌለ በመረዳት በሕግና ሥርዓት እንዲሁም በይቅርታ አገራቸውን በጋራ ለማነፅና ለመገንባት ከስምምነት እንደሚደርሱም ይጠበቃል።

ይሄን መሰሉ በአገራችን የተፈጠረ ምቹ ሁኔታና ዕድል ከጦርነት ጋር በተያያዘ ባለፉት አራትና በላይ ዓመታት የገጠሙንን አገራዊ ችግሮች ብቻ ሳይሆን በአደገኛ አደንዛዥ ዕጽና የአልኮል ይዘት ባላቸው መጠጦች የሱስ ተገዥ ለመሆን የተዳረገውን አምራች ወጣት የኅብረተሰብ ክፍል ችግር ለመፍታትም ይመቻል።

የሰላም አየር ተንፍሰን ወደ ልማት መዞራችንን የምናረጋግጠው ይሄን የወጣቱን ችግር በመፍታት በአገሩም ሆነ በአህጉሩ አፍሪካ ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊና ውሳኔ ሰጪ ማድረግ ስንችል ነው። ሰፊ ጊዜውንም ሆነ ትኩስ ጉልበትና ኃይሉን እንዲሁም ብሩህ አእምሮና የፈጠራና የምርምር ብቃቱን ለሰላምና ለአገር ግንባታ ማዋል እንዲችል ስናደርግ ነው። የስብዕና ግንባታ ማዕከላትን ስንገነባለትና ከአልባሌ ቦታ መዋልና ከጥፋት ስንታደገው ነው።

እንደሚታወቀው ወጣቶች ባለ ብሩህ አእምሮና የምርምርና የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው በመሆኑ አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር ብቃታቸውን በመጠቀም ለአገር ብልጽግና የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የላቀ ነው። ይሁንና የወጣቶችን ዕምቅ አቅም ለመጠቀም በዕውቀት፤ በአመለካከትና በክህሎት እንዲዳብሩና ስብዕናቸውን መገንባት የግድ ይላል። ይህ ሳይሆን ሲቀር በቀላሉ ለችግር በመጋለጥ ወደ ጥፋትና አፍራሽ ድርጊቶች የመግባት ዕድላቸው የሰፋ መሆኑ ይታመናል።

ለዚህ ደግሞ በተለይ በትምህርት ተቋማት ዙሪያ ያሉ ጫት ቤትና ሲሻ ቤቶች እንዲሁም በሻይ ቡናና ምግብ ሳቢያ የአልኮል ይዘት ያላቸው መጠጦች፤ ዝሙትና ሌሎች ወጣቱን ለጥፋት የሚዳርጉ ተግባራት በስውር የሚከውኑ ቤቶችን ጠራርገን ማጥፋት ይኖርብናል። በዚህ እርምጃ ሱስ በማስያዝ የወጣቱን ጊዜ በከንቱ የሚያባክኑና ከውጭ ለመጡና ከባህላችን ለሚጣረስ ተግባር የሚዳረጉ የወሲብ ቤቶችም የግድ መወገድ አለባቸው።

አገር አቀፍ የንቅናቄ ጥሪውን ተከትሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዙሪያው እንዲህ ዓይነት እኩል ተግባራት በመከወን ገንዘብ የሚያካብቱ ትውልድ ገዳይ ቤቶችን በመጠራረግ ቁርጠኝነቱን አሳይቶናል። ሌሎች እንደ አገር ያሉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደሮችም የዩኒቨርሲቲውን ፈር ሊከተሉ ይገባል። ሁሉም ወረዳና ክፍለ ከተማ እንዲሁም ከተማ አስተዳደሮች በየአካባቢያቸው በየዕለቱ እየተፈለፈሉ የሚያድሩትን እነዚህን እኩይ ተግባር መከወኛ ቤቶች በዝምታ ሊመለከቷቸው ፈፅሞ አይገባም። ንቅናቄው ግቡን ሊመታና ውጤታማ ሊሆን የሚችለውም በጋራ ተሳትፎ ተግባር ድምር መሆኑ ሊታወቅ የግድ ይላል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የሹራብ ካባን በፋሽን

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ከአገራችን የእደ ጥበብ ውጤቶች አንዱ ሆኖ የቆየው የሹራብ ሥራ አብዛኛውን ጊዜ በሴቶች ሲከወን እንደኖረም ይታወቃል። ይህ የሹራብ ሥራ ከቴክኖሎጂ ጋር እየተዋደደ መጥቷል፤ በእጅም ሆነ በማሽን በተለያየ ዲዛይን እየተመረተ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ የሹራብን ዲዛይን ዘመኑን በሚመጥን መልኩ በዲጂታል መሣሪያ ዲዛይን አድርጎ መሥራት እየታቻለ ነው። ሹራብን በእጅ ከመሥራት ይልቅ በዲጅታል ማሽን ተጠቅሞ መሥራት ውስጥም ተገብቷል። በዚህም በሹራብ ሥራ ላይ የበለጠ ለውጦች እየታዩ መጥተዋል።

አሁን ላይ ሹራቦች ቀደም ሲል ከነበረው የተለመደ አሠራርና ዲዛይን ወጣ ባለመልኩ ጥራታቸውን ጠብቀው የትም ቦታ ላይ ሊለበሱ በሚችሉበት ሁኔታ ዲዛይን ተደርገው ተመርተው ለገበያ እየቀረቡ ናቸው። ዘመናዊ ፋሽንን በተከተለ መልኩ የሚሠሩ እነዚህ ውብና ማራኪ የሹራብ አልባሳት ከመቼውም ጊዜ በላይ ተወዳጅነታቸው እየጨመረና እየተለመዱ መምጣታቸውን የዘርፉ ባለሙያዎችም ይመሰክራሉ።

የሹራብ ሥራ ለመሥራት ንድፍ ከማውጣት ጀምሮ ብዙ ጊዜ የሚወስድና ልፋትን የሚጠይቅ መሆኑን ባለሙያዎቹ ጠቅሰው፣ ተሠርተው ሲለበሱ ግን የሚያምሩና ረጅም ጊዜ ሊቆዩ የሚችሉ እንደሆኑም ይናገራሉ።

የሰላማዊት ሹራብ ማምረቻ ድርጅት ባለቤት የሆነችው ወይዘሮ ሰላማዊት ሁሴን በሹራብ ሥራ ላይ ቆይታለች። እሷ እንደምትለው፤ በሹራብ የሚሠሩ ለወንዶች፣ ለሴቶችና ለሕፃናት የሚሆኑ ዩኒፎርሞችን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት የሹራብ ሥራዎች ድርጅቷ ይሠራል። ወይዘሮ ሰላማዊት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ትኩረቷን በሹራብ በሚሠሩ የሴቶች ካባዎች ላይ አድርጋለች። እነዚህ ከሹራብ የሚሠሩ የሴቶች ካባዎች እንደ ባህል አልባሳት ሁሉ ጥለት እንዲኖራቸው ተደርጓል።



**የሴቶች የሹራብ ካባ ተፈላጊነት እየጨመረ መጥቷል**

ካባዎቹ ቀደም ሲል ያልተለመዱ ከሹራቡ ዳር ዳር ላይ የባህል ጥለት ያላቸው ለየት ያሉ ናቸው የምትለው ወይዘሮ ሰላማዊት፣ የሹራብ ካባው ለወጣቶችም ሆነ ለአዋቂ በሚሆን መልኩ እንደሚዘጋጁም ትናገራለች። ካባውን ወጣቶች በቀበቶ አድርገው ከታይት ጋር ይለብሱታል፤ እናቶች ደግሞ እንደ ካባ ይደርቡታል ነው የምትለው።

ካባዎቹ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም ባይለመዱም አሁን ላይ ተፈላጊነታቸው እየጨመረ መምጣቱን የምትጠቁመው ሰላማዊት፤ የሹራብ ካባ ምርቶቿን ፖስታ ቤት፣ ሽሮሜዳ፣ ኮልፌና መርካቶ አካባቢ ለሚገኙ የአገር ውስጥ ተረካቢዎች ታቀርባለች። አብዛኛዎቹን ካባዎች ፖስታ ቤት አካባቢ የሚገኙ መደብሮች ከሷ ተረክበው ወደ ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ለዲያስፖራው እንደሚሸጡት ገልጻለች።

"በቅርቡ በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው ኤግዚቢሽን ላይ ያገኘኋቸው ውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ኒውዮርክ ላይ እኔ ዲዛይን የማደርገውን የሹራብ ካባ በኦንላይን መግዛታቸውን አውግተውኛል" የምትለው ሰላማዊት፤ ካባው እንደተመቻቸውና ደስተኛ መሆናቸውን በመግለጽ በድጋሜ ገዝተው መሄዳቸውንም ትናገራለች። ሰላማዊት የሹራባ ካባው ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚላከው በአንዲት ግለሰብ መሆኑን ጠቅሳ፣ ግለሰቧ በኦንላየን እየሸጠች መሆኑን ነው የምትናገረው፤ ካባውን በአሁኑ ወቅት በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በእጅጉ እንደሚፈልጉት ትጠቁማለች።

የምዕራባውያንን ተፅእኖ ለመከላከል በኢትዮጵያውያን ተካሂዶ በነበረው "የ#በቃ" (#NOMORE) እንቅስቃሴ ላይ የምትታወቀው ጋዜጠኛ ሐርሜላ አረጋዊ ለብሳው እንደነበር አስታወሳ፤ ሐርሜላ ካባውን በፖስታ ቤት በኩል እንዳገኘችው ማወቋን ትገልጻለች።

"የካባ ሥራዎችን ከመጀመሬ በፊት ከባለቤቴ ጋር በመሆን ብዙ የሹራብ ሥራዎችን እንሰራ ነበር" የምትለው ሰላማዊት፤ ቀደም ሲል በሁለት መልክ ከሹራብ ካባ መሥራት የተለመደ እንደነበር ታስታውሳለች። ከዚህ በተሻለ መልኩ ባህላዊ ይዘት እንዲላበስ አድርገን ብንስራው የሚለውን ሀሳብ በማፍለቅ ባለቤቷ ዲዛይኑን እንደሠራው ገልጻ፤ ውጤቱ ሲታይ በጣም ቆንጆ እንደነበርና ወደ ገበያ ሲያወጡት በቶሎ ተቀባይነት እንዳገኘም ነው የተናገረችው። ካባው ለሕፃናት፣ ለወጣቶች እና ለአዋቂም በሚሆን መልኩ እንደሚመረት ትገልጻለች።

ሰላማዊት እንዳለችው፤ የሹራብ ካባውን ተደራሽ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። በ2014 ዓ.ም ከግንቦት 1 እስከ 5 በልማት ባንክ የተሰጠውን ሥልጠና በመወሰድ አምስት ተጨማሪ ማሽን ለመግዛት የሚያስችል ፕሮፖዛል አቅርባለች፤ ማሽኖቹን ስታገኝ ደግሞ ካባውን በጥራት በማምረት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ሀሳብ አላት። ይህ ሀሳብ እውን ሆኖ ሲሳካ ደግሞ የሹራብ ካባው ተደራሽነት እየሰፋ ይመጣል።

ሰላማዊት እንደምትለው፤ ሹራብ በማሽን የሚሠራ ቢሆንም፣ ብዙ የሰው ኃይል ያስፈልገዋል። አሁን ላይ ሰባት ቋሚ ሠራተኞችና ከ15 በላይ ጊዜያው ሠራተኞች አሏት። ካባውን ለመስራት የምትጠቀምበት ዲጅታል ማሽን ኮምፒዩተራይዘድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ሁሉም ሰው የሚያወቀው አይደለም። ስለዚህ ማሽኑን ለመጠቀም እንዲቻል የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። አሁን ላይ ሦስት ሰዎች ስልጠና እንዲያገኙ እየተደረገ ነው።

ዲጅታል ማሽኑ ላይ መሥራት ያለበት ሰው የተማረና ሥልጠና የወሰደ ማሽኑን በሚገባ በማወቅ አስፈላጊውንም የመፍትሔ አቅጣጫ እያስቀመጠ የሚመጣ መሆን አለበት የምትለው ሰላማዊት፤ ዲጅታል ማሽኑ እንከን ሲያጋጥመው ድምጽ ያሰማል፤ ከዚያም ያጋጠመውን ችግር ስለሚፅፍ ያንን አንብቦ መረዳት የሚችል የሰለጠነ ሰው ያስፈልጋል ትላለች። ተጨማሪ ዲጅታል ማሽኖች ወደ ሥራ ሲገቡ ደግሞ በዚያው ልክ የሰው ኃይል ማሰልጠንና ብቁ ባለሙያ ማፍራት እንደሚቻል ትገልፃለች።

"የሹራብ ሥራውን አሃዱ ብለን ስንጀምር ቀደም ሲል ለሥራው የሚያገለግለው በጣሊያን ጊዜ የነበረ ማሽን በዲጅታል ማሽን እንዲተካ በማድረግ የተሻለ ነገር ለመፍጠር አንድ እርምጃ ከፍ ያለ ነገር ማበርከት ብንችል ብለን አስበን ነው" የምትለው ሰላማዊት፤ ልጆቻችንን ደግሞ ከእኛ በተሻለ መልኩ ከፍ ካደረጉት የአገራችንን የሹራብ ሥራ አንድ ደረጃ ማሳደግ እንችላለን ስትል ትገልጻለች።

«የሹራብ ካባን ለመሥራት በመሠረታዊነት የሚያስፈልገው ጥሬ ዕቃ የሱፍ ክር ነው» የምትለው ሰላማዊት፤ የሱፍ ክሩን በቋሚነት ከውጭ የሚያስመጡ እንዳሉ ጠቅሳለች። እስካሁን ባለው ሂደት የጥሬ ዕቃ የዋጋ ጭማሪ እንጂ የጥሬ ዕቃ የአቅርቦት እጥረት እምብዛም እንዳላጋጠማት አስረድታለች።

ሙያው በትምህርት ሳይሆን በልምድ ያገኘችው እንደሆነ የምትናገረው ሰላማዊት፤ የሹራብ ሥራ ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ሙያውን በተለያየ መልኩ ዲዛይን በማድረግ እያሳደገችው መጥታለች። ሙያው በትምህርትም የተደገፈ ቢሆን ደግሞ የተሻለ መሥራት እንደሚቻል ነው የተናገረችው። እርሱን ለማሳካት ጥረት እያደረገች እንደምትገኝ ትገልጻለች። የሹራብ ሥራውን የጥራት ደረጃ በመጨመር ወደ ውጭ አገር ኤክስፖርት ለማድረግ ሙከራ እያደረገች መሆኗን ገልፃም ሀሳቧ ታጠቃልላለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## አንድ ወደፊት - አሥር ወደ ኋላ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ነዋሪው ዓመታትን በጥያቄ የተጋበት ጉዳይ ዘንድሮ ዕልባት ማግኘቱ አስደስቶታል። አብዛኛው በወጣ በገባ ቁጥር ዓይኑን ከመንገዱ አይነቅልም። በየቀኑ የግንባታውን ለውጥ በአትኩሮት ይቃኛል። የታከለውን አዲስ ነገር እያስተዋለ ቀጣዩን በጉጉት ይመኛል።

ማልደው በስፍራው የሚደርሱ ሠራተኞች ለነዋሪው የዓይኑ ርሀብ ናቸው። ከሰዓታቸው አለፍ ካሉ ሁሉም ደስ አይለውም። በርከት ብለው ሲመጡ ፈገግታው ይበራል፣ መቆፈሪያ ቡልደዘራቸውን፣ አካፋ ዶማቸውን ማየት የልብ ደስታው ከሆነ ቆይቷል። የእነሱ ድካም የአብዛኛው ሰው ብርታትና ተስፋ ነው። የእነሱ መታየት ለነገው ዓለም ብርሃን ነው።

ለአካባቢው ከዚህ እውነታዎች ማዶ ነገ ሲታሰብ ብዙ ትርጉሞች አሉት። ሁሉም ትናንት የሆነበትን አይረሳም። በዚህ ጎዳና የተከለሉ፣ በጥሻው የተደበቁ፣ ጨለማን የተተገኑ ጨካኞች ብዙ ፈጽመውበታል። ከጉድባው ተሸሽገው፣ ኪሱን አራቁተዋል፣ ንብረቱን ዘርፈዋል። አለፍ ሲልም ስለት ድንጋይ ጨብጠው ነፍስ የቀጠፉ፣ አካል የጎዱ አይጠፉም። ዛሬ ደግሞ ለአካባቢውና ዙሪያው ደማቅ ፀሐይ የወጣ፣ መልካም ቀን የመጣ ይመስላል። የነዋሪው የዓመታት ጥያቄ ምላሽ አግኝቶ የመንገዱ ግንባታ ተጀምሯል። እንዲህ በሆነ ማግስት የነበረው ደስታም ‹‹አጀብ›› የሚያስብል ነበር።

ይህ ያልተመቸ መንገድ ለዓመታት በርካቶችን አመላልሷል። መኪኖችን፣ ባጃጆችን፣ ጋሪዎችን በእኩል አጋፍቷል። የአካባቢው ህልም ይህ አልነበረም። መንገዱ እንደታሰበው በአስፓልት ተለውጦ፣ ማየትን ሲሻ ኖሯል። መብራቱ ገብቶለት፣ የተዘጉት ንግድ ቤቶች በወጉ ሥራ ጀምረው መመልከትን ተመኝቷል።

ይህ ይሆን ዘንድ ነዋሪው ኮሚቴ ያላዋቀረበት፣ በየስብሰባው መድረክ ያልተናገረበት፣ ያልጮኸበት ጊዜ የለም። የመንገዱ ጉዳይ ሁሌም የዓመቱ ስብሰባዎች አጀንዳ መክፈቻና መዝጊያ ነው። ጥያቄ ይነሳበታል፣ አስተያየት ይታከልበታል፣ በመጨረሻ የተለመደው ተስፋ ተቋጥሮበት በይደር ይታለፋል።

የሚገርመው የነዋሪው ተስፋ አለመቁረጥ ነው። ሁሌም ከመንገዱ መገንባት ጋር የሚሠራውን ድንቅ ተግባር ከማለም አይቦዝንም። አካባቢው የጋራ መኖሪያ እንደመሆኑ የነገው ትልሙ ከዕድገት ጋር የተያያዘ ነው። በነዚህ ሕንፃዎች ስር በጨረታ የተገዙት የንግድ ቤቶች ለዓመታት ከታለመላቸው ዓላማ ውጪ ባክነዋል። የዛሬን አያድርገውና ቤቶቹ ከፍ ባለ ዋጋ ለገዢዎች ሲተላለፉ የመንገዱ አስፓልት መሆን ታሳቢ ተደርጎ ነበር።

ዛሬ ግን አብዛኞቹ ስማቸውን አልተሸከሙም። እንኳን ለንግድ ለመኖሪያነት አልተመረጡም። ሁሉም በሚባል መልኩ የጥርጊያውን አቧራ እንደ ጋቢ መከናነብ ግዴታቸው ሆኗል። በጋው አልፎ ክረምቱ ሲመጣ ደግሞ ጭቃ፣ ዝናብና ጎርፍ ሳይጎበኛቸው አያልፍም። ችግሩ በእነሱ ብቻ አይቆምም። የዝናቡና የጎርፉ መጥለቅለቅ የሕንፃውን አጠቃላይ ህልውና ለከባድ ስጋት ሲያጋልጠው ኖሯል።

አሁን ደግሞ ነዋሪው ያላሰለሰ ምስጋናና ውዳሴ በአፉ ይመላለስ ጀምሯል። የዓመታት ደጅ ጥናቱ፣ ጥያቄና ልመናው ጫፍ ይዟልና ግንባታውን የሚያየው በተለየ ስስትና አትኩሮት ነው። ይኸው እንግዲህ ትራክተር፣ ቡልደዞር፣ ሲኖትራክ፣ ግሬደር መርመስመስ ይዘዋል።

ማለዳውን ብቅ የሚለው አንገተ ረጅሙ ሎደር ጎንበስ ቀና የሚለው ብቻውን አልሆነም። ነዋሪውም አብሮት በድካም ሲዋትት ይውላል። ለሥራው አንዳች ነገር ባይፈይድም ሁሌም ለበጎ ሀሳብ ከአካባቢው አይርቅም።

የግንባታ መኪኖቹ ድንጋዩን ዘርግፈው፣ ጠጠሩን አፍሰው መንገዱን ባሰለጡት ቀን ሁሉም የዕድገቱን ለውጥ እያሰበ የቀጣዩን ቀን ውሎ ያልማል። ከዚህ በኋላ ሊቀር የሚችለው ሥራ ጥቂት እንደሚሆን የሚገምተውም ይበዛል። ማግስቱን ዓይኑን ከስፍራው የሚጥለው ተመልካች እንደልማዱ የመኪኖቹን መምጣት ሲጠብቅ፣ ሲናፍቅ ያረፍዳል።

መንገዱ ደግሞ እንደሰሞኑ አልሆነም። ሆዱ እንደተገመሰ፣ ጎኑ እንደተቆረሰ ያለአንዳች ድምጽ ረጭ ብሎ ይውላል። ተመልካቹ ተስፋ አይቆርጥም። ቀጣዩን ቀን በጉጉት ይጠብቃል። አሁንም አንዳች አካል ዝር ሳይል መዋል ማርፈዱን ያስተውላል። አንድ ቀን ብቅ ያሉት የመንገዱ ሠራተኞች ዝር ሳይሉ አስር ቀናት ይቆጠራሉ። ይቀጥላል። ቀናቶች በእጥፍ ይጨምራሉ።

የነዋሪው ዓይኖች ፈጽሞ ተስፋ አይቆርጡም። ባሻገር እያስተዋሉ፣ የመኪኖቹኑ መምጣት፣ የሠራተኞቹን ድረስ ይናፍቃሉ። ተናፋቂዎቹ ግን ጅምራቸውን እንዳዝረከረኩት ድራሻቸው ይጠፋል።

ቀናት ለወራት እየተጠጉ ይገሰግሳሉ። ተፈላጊዎቹ ብቅ ዝር አይሉም። ወቅቱ እንደሁ ሰዓቱን አይስትም። ፀሐይ ትደበዝዛለች፣ ዳመናው ያንዣብባል፣ ዝናቡ ማከፋት ይጀምራል። ካፊያው አምርሮ ዶፍ ዝናቡ ሲቀጥል፣ የከረመው ውሃ ደራሽ ወንዝ ሆኖ በጎርፍ መጥለቅለቁ ይፋጠናል። ይህኔ ጠፍተው የከረሙት ተናፋቂዎች በድንገት ከቡልደዘር፣ ሎደራቸው ጋር ይከሰታሉ።

የሚገርመው ሲመጡ ባዷቸውን አይደለም። ሲኖዎቹ ድንጋይ አሸዋ ጭነው፣ አይሱዚዎቹ ጠጠር ኮረት አጭቀው ነው። ቀድሞ የመጣው ግብአት አፈርና ጭቃ ሆኗል። እነሱም አይተዋል። ደንታ አይሰጣቸውም። የጫኑትን ዘርግፈው ሌላ ክምር ሊያመጡ በፍጥነት ይከንፋሉ።

አሁንም ነዋሪው የመጣውን አይቶ ሌላን የለውጥ ቀን ይናፍቃል። ቀናት እንደዋዛ አልፈው ወራት መቆጠር ይይዛሉ። አሸዋው ኮረትና ድንጋዩ እየታየ ደልዳላ መሬት ይሆናል። አካባቢው በውሃ ጭቃ ይጨቀያል፣ እግረኞች መንገድ ፍለጋ ሌላ መንገድ እያበጁ አዲስ ጎዳና ይቀይሳሉ።

ደግሞ በሌላ ቀን ተናፋቂዎቹ እንደዋዛ ብቅ ይላሉ። ሳር የበቀለበትን ደልዳላ መንገድ በመዛቂያቸው ቆፈር ቆፈር አድርገው መለስ ቀለስ ይሉና ድራሻቸው ይጠፋል። ጥቂት ቀናት ቆይተው ያው ዝናቡ ሲመጣ ትላልቅ ቱቦዎችን ይዘው ይደርሳሉ። ተስፋ የማይቆርጡ ፊታቸው በፈገግታ በርቶ መንገዱ ሊያልቅ መሆኑን ያስባሉ።

ተናፋቂዎቹ አንድ ወደፊት አስር ወደኋላ ማለታቸውን አይስቱም። ግዙፎቹን ቱቦዎች ግራና ቀኝ ከምረው፣ ደርድረው ይጠፋሉ። ቱቦዎቹ ጥቂት ቀናት ቆይተው የጎዳና ልጆች ማደሪያ፣ የማጅራት መቺዎች መደበቂያ ይሆናሉ። ቋጥኝ የሚያህሉት ቱቦዎች ከፍ ያለ ገንዘብ የወጣባቸው የአገር ሀብቶች እንዲህ መባከናቸውን ያዩ እርር፣ ትክን፣ ድብን ይላሉ።

ጉደኞቹ ተናፋቂዎች ይህም ስሜት አይሰጣቸውም። ከጣሏቸው ወራት ያስቆጠሩትን ግዙፍ ቱቦዎች እንደነገሩ በየጉድጓዱ ወሽቀው ሌሎች ቀናትን በዝምታ ያደፍጣሉ።

እነሆ ! ዛሬም ይህ ተስፈኛ መንገድ ሌላው ክረምት ደርሶበታል። ከሰሞኑ የተዘረገፈለት ትላልቅ ኮረትና ድንጋይ ተከትሮ መጪውን ጎርፍ ለመስኖ ያዘጋጀው ይመስላል። ከሰሞኑ ብቅ ያለ ባለግሬደር፣ ዝር ያለ ባለ ሎደር የለም። አሁንም ዝናቡ፣ አይቀሬው ክረምቱ ‹‹መጣሁ፣ደረስኩ›› እያለ ነው።

ብቅ እያሉ የሚጠፉት የመንገዱ ባለሙያዎች ንብረቱን ፣ መንገዱንና የአገር ፣ ሀብቱን እንደዋዛ በትነው ኮሽታቸው ጠፍቷል። አንድ ወደፊት የመራመዳቸው እውነት ተጠናክሮም እርምጃቸው የኋሊት በአስር ተባዝቷል። ‹‹አንድ ወደፊት አስር ወደኋላ›› እንዲሉ ።

## ነፃ ሃሳብ

# የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ የአዲስ እሳቤና የተሀድሶ ንቅናቄ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የሰው ልጅ ትልቁ ፍላጎት ሰላም ነው። እንደፍላጎቱ የሆነለት ግን የለም። ለዘመናት በጦርነትና በእርስ በርስ ግጭቶች ዋጋ ሲከፍል የኖረ ነው። እውነትና ሚዛናዊነትን ባስቀደመ መልኩ ጠብ ጫሪዎች ሲቀጡና ተጎጂዎች ሲካሱ የሚያሳይ ሥርዓት እምብዛም ነው።

ይሄን የፍትህ ጥያቄ ለመመለስና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚሠሩ የፍትህ ፖሊሲዎች መካከል የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ቀዳሚው ነው። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አሁን ላለችው ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ የሆነበት ወቅት ነው። በጦርነትና ማንነትን መሠረት ባደረጉ አለመግባባቶች የደረሱብን በደሎች ከትናንት ወደ ዛሬ የመጡ አገራዊ ገበናዎቻችን ናቸው። እነዚህ ገበናዎቻችን እንዲታከሙ ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ የፍትህ ሂደት አስፈልጓል።

በዓለም ላይ በብዙ አገራት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ተግባራዊ ተደርጓል። ከእርስ በርስ ጦርነት፣ ከግጭትና ከብሔር ፖለቲካ እንዲሁም በፖለቲካና በዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ላይ ትርጉም ያለው ውጤት ያመጡ አገራት ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። የትግበራ ሂደቱ ሰላምና ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር እውቅና የተሰጠው ሲሆን የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ በአፍሪካ ኅብረት በኩል ይሁንታን ያገኘ የተሀድሶ ንቅናቄ ነው።

በ2011 ዓ.ም በመዲናችን አዲስ አበባ የጸደቀው የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ አገራት የተለያዩ የፖሊሲ እርምጃዎችን እና ተቋማዊ አሠራሮችን በመጠቀም የመብት ጥሰቶችን ጨምሮ ክፍፍሎችንና አለመግባባቶችን እንዲሁም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊ ሂደት እንደሆነ ገልጸዋል።

ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ታትኮ መነቃቃት የጀመረው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ተዓማኒነትና ይሁንታን አግኝቶ በተለያዩ የዓለም አገራት በተለያየ ይዘት ተግባራዊ ተደርጓል። ፍትህንና ተጠያቂነትን እንደመርህ አንግቦ ሲንቀሳቀስ የነበረው የፍትህ ሥርዓት ለብዙዎች የነፃነት እና የዴሞክራሲ ጥያቄ መልስ የሰጠ ሆኗል።

ባለፈው ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያም በተለያዩ ጊዜያት የሽግግር ፍትህ ሂደት አላባዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ተደርጓል። ነገር ግን፣ ከስልቶቹ በተጨማሪ አላማና ግቡን የሚቃኝ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ በበቃና በነቃ መልኩ ስላልነበር የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም።

ከዚህ ልምድ በመነሳት፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን እና ሂደቶችን ባገናዘበ መልኩ ያሉና የነበሩ፤ ወደ ፊትም የሚኖሩ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ እንደአዲስ እየተንቀሳቀስን ያለንበት ሂደት ነው ያለው። ይህ አላማ እንደ አገር ግቡን እንዲመታና የሚፈለገውን የፍትህና የተጠያቂነት ውጤት እንዲያመጣ ጥናት ባደረጉ ባለሙያዎች የመነሻ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ ውይይት ተደርጎበታል።

ውይይት ከተደረገባቸው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች መካከል መጀመሪያ ላይ የተቀመጠው የሽግግር ፍትህን ታሪካዊ አመጣጥ እና አገራችን ካለችበት ወቅታዊ ችግር አንጻር የፖሊሲውን አስፈላጊነት የሚቃኝ ነው። ቀጥሎ በባለሙያ ውይይት የተደረገበት ምክረ ሀሳብ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን በተመለከተ በአገራችን ያሉትን አማራጮች እና ምክረ ሀሳቦች ያቀፈ ሲሆን በመጨረሻም የፍትህ ፖሊሲው ሊመራባቸው የሚገቡ መርሆችና የአደረጃጀት አማራጮችን የቃኘ ነበር።

ሦስቱን የመወያያ ሀሳቦች ብንመለከት አሁን ላሉብንም ሆኑ ወደ ፊት ለሚፈጠሩብን ችግሮች የመፍትሄ አካል ሆነው እናገኛቸዋለን።

በተደጋጋሚ እንደ ጠቀስነው፣ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት የሚያጠያይቅ ጉዳይ አይደለም። በተለይ እንደ እኛ አገር ባሉ፣ ብሔርን መሠረት አድርገው ለሚነሱ ግጭቶችና አለመግባባቶች ከዚያም አለፍ ሲል በፖለቲካው በኩል ለምናየው የመብት ጥሰት ተጠያቂነትን የሚያሰፍን ሆኖ እናገኘዋለን።

የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ተጠያቂነትን ከማስፈን አንጻር «የተሻለ» ያለውን አማራጭ ይዞ ብቅ ባለበት በዚህ ሰሞን በበዳይና በተበዳይ መካከል ሚዛናዊ ዳኝነትን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። ከዚህ በፊት በነበረው ሥርዓት ክስና ቅጣት ላይ የተመሠረተ አሠራር ሲኖረው ይህን ተግባር እንዲያቀላጥፉ ጊዜያዊ ፍርድ ቤቶችና ዓለምአቀፍ ተቋማት የተቋቋሙ ሲሆን፣ ይህ ዓይነቱ አጥፊዎች ላይ ብቻ የተመሠረተው የፍርድ ሂደት መሠረታዊ ጉድለት እንዳለው በመረዳት አዲስ አሠራር መከተልን ግድ ብሏል።

አጥፊዎች ላይ ብቻ በማተኮር አገር ለማዳን፣ ዴሞክራሲ ለመገንባት አለመቻላቸው፣ ስለሕግ ጥሰቱ በቂና መረጃን መሠረት ያደረጉ ማስረጃዎችን አለማዘጋጀታቸው ከዚህ ከፍ ሲልም ማህበረሰቡን የመከታተል አቅማቸው ውስን መሆኑ አዲስ አቅጣጫን እንዲከተሉ አስገድዷቸዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ሌሎች መሠረታዊ ጉድለቶችንም መጥቀስ ይቻላል። ሁሉንም አጥፊዎች ለፍርድ ማቅረብ የማይቻል መሆኑና የተወሰኑትን ብቻ የሚቀጣ የፍትህ ሥርዓት በመሆኑ የተሻሉ አማራጮችን እንዲያይ ዕድል ፈጥሮለታል። ክስ ላይ ብቻ የተመሠረተው የፍትህ ሂደት ከክስና ከቅጣት ከካሳም ባሻገር ለዘላቂ ሰላምና ለዴሞክራሲ ግንባታ ቅድሚያ የሚሰጥ ዘመናዊ አሠራርን ይዞ ብቅ ብሏል።

ከዚህ በኋላ ባለው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ የምንዳኘው እንዳለፈው ጊዜ ቅጣት ላይ ብቻ ሳይሆን ምሉዕ በሆነና ይሁንታን ባገኘ የፍርድ ሂደት በኩል ነው። እንደ አዲስ በሥራ ላይ የዋለውና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው የፍርድ ሂደት እውነትን መሠረት አድርጎ የሚጀምር እና በዚያ እውነት መሠረት እርቅና ካሳ፣ ቅጣትና ተጠያቂነት የሚቀጥሉበት አሠራር ነው።

በአገራችን የነበረውን የሽግግር ፍትህ ተሞክሮ ብዙ ጥያቄዎች የሚነሱበት እንደነበር የሚታወቅ ነው። ሂደቱ ነበረ፤ ይሁን እንጂ ሂደቱ እንደመነሻ አላማው የሚፈለገውን ለውጥ ያመጣ አልነበረም። በጦርነት እና በፖለቲካ ሽኩቻ፤ በመሰል ሁኔታዎች የተነሱ በደሎችንና ጭቆናዎችን፣ ጥያቄዎችንና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አይቶና መርምሮ እውነትን መሠረት ባደረገ መንገድ ፍትህንና ተጠያቂነትን፤ እንዲሁም፣ ከዚያ አለፍ ሲል በእርቅና በምህረት ላይ ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ አልነበረም።

ያለፉ የፖለቲካ ሥርዓቶቻችንንና በሕዝብ ላይ ያደረሱትን መጠነ ሰፊ የመብት ጥሰት ብናነስ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ከስም የዘለለ ምንም እንዳልነበር እንደርስበታለን። ያለፉትን ስልሳ አመታት የፖለቲካ ሂደት ብናስተውል ሥልጣን የተያዘውና ከሥልጣን የሚለቀቀው በብዙ ሞትና በብዙ የመብት ጥሰት በኩል ነበር።

የአጼው ሥርዓት ያበቃው በመንግሥቱ ኃይለማርያም በተመራ የደርግ መንግሥት ነበር። ደርግ ኃይለሥላሴን ገፍትሮ ወደ ሥልጣን ሲወጣና ከወጣ በኋላም የታሠሩትንና የተረሸኑትን እንዲሁም ደብዛቸው የጠፉን ባለሥልጣናት ትተን በሕዝብ ላይ ብዙ በደሎችን ፈጽሟል።

ከደርግ በኋላ የመጣው ኢህአዴግም የደርግ መንግሥትን ተጠያቂ ለማድረግ በ1983 ዓ.ም የሽግግር መንግሥት የመሠረተ ሲሆን፣ ሕግና መርህ ያልተከተለ እንደነበር ይተቻል። የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው እንዲተች ያደረገው ዋናው ነገር ከላይ ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት እውነትን መሠረት ያላደረገ መሆኑና እርቅና ምህረትን ያላካተተ ከመሆኑም በተጨማሪም ብዙኃኑን ማኅበረሰብ ትቶ ባለሥልጣናት ላይ ብቻ ማተኮሩ እንደሆነ ይነገራል።

ከዚህ ባለፈ እንዳለፈው መንግሥት ሁሉ የኢህአዴግም መንግሥት በመብት ጥሰት ስሙ ከመነሳት አልዳነም። አሁን ያለው መንግሥትም ፍጹምና እንደሌለው አንድ ፓርቲ በሽግግር ፍትህ በኩል የሚታይ ሙገሳና ወቀሳ ይጠብቀዋል ባይ ነኝ። ፖለቲካችን ጠርቶ አያውቅም።

በብሔር ስም መነሻውን ያደርግና መድረሻውን በሕዝብ እንባ ይደመድማል። ባልጠራ ፖለቲካ ውስጥ የመብት ጥሰት ሁሌም አለ። የሽግግር ፍትህ ያስፈለገበት አንዱና ዋናው አላማ ደግሞ ባልጠራ ፖለቲካ ውስጥ የተፈጸሙና የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶችን መመርመርና ፈትሾ ተጠያቂነትን ማስፈን ነው።

የቅርብ ጊዜ ትውስታችን የሆነው በ2010 ዓ.ም በአገራችን የተፈጠረውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ የመጣው የሽግግር ፍትህ እሳቤ ነው። ገዢው ፓርቲ ያለፉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ማንነትና ዘርን መሠረት ያደረጉ ቁርሾዎችና መገፋፋቶች በእውነት ሚዛን ላይ አርፈው በእርቅና በፍትህ በዳይ እንዲጠየቅ፤ ተበዳይ እንዲካስ እውነት መር በሆነ የፍትህ ሂደት ሰላም እንዲሰፍን የሽግግር ፍትህ ርምጃዎችን እንደወሰደ አይዘነጋም።

ከዚህ ከፍ ባለ መልኩ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ብርቅ የሆነና ተሰምቶ የማይታወቅ የይቅርታ ድምጽ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ አንደበት ተሰምቷል። «ላጠፋነው ጥፋት ሁሉ ይቅርታ እጠይቃለሁ» ሲሉ በትናንት ፖለቲካ ውስጥ የነበረውን በማስታወስ ይቅር በሉኝ ብለዋል።

ይሄን የይቅርታ ድምጽ ተከትሎ የእርቀ ሰላም ኮሚሽን ተቋቁሟል። የሰላም ሚኒስቴር ተመስርቷል። እንዲሁም፣ ለውጥ የሚያመጡ የሕግና የተቋማት ማሻሻያዎች ተደርገዋል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ግን እንደ አገር የሚጠበቅብንን ለውጥ አላመጣንም። ዛሬም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ስንል ዳግመኛ በምክረ ሀሳብ መጥተናል።

ካለፉት ስህተቶቻችን ተምረን በዚህ የሽግግር ፍትህ ጅማሬ ተጠያቂነትን ማስፈን የመጨረሻ ዕድላችን ቢሆን እመኛለሁ። በአገራችን እንደችግር ከሚነሱ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ጀምሮ ማቆም ነው። እንደ አጀማመራችን የጨረስነው የለንም። የሽግግር ፍትህ አሁን ለሦስተኛ ጊዜ መነሳቱ ነው።

እንደ አጀማመራችን ፍጻሜ ላይ የበረታን ቢሆን ኖሮ ከማንም ቀድመን ለውጥ የምናመጣ ሕዝቦች እንሆን ነበር። አብዛኞቹ ጉዳቶቻችን ጀምረን ካቆምናቸው ጉዳዮች የተሳቡ ናቸው። ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት መጀመር ጥሩ ሆኖ ሳለ የሚፈለገው የሚገኘው ግን በመጨረስ ውስጥ ነው።

ሌላውን ትተን ለአገራችን የመጀመሪያ የሆነውን እና ብዙ ችግሮቻችንን ይቀርፍልናል ስንል እምነት የጣልንበት «የእርቀ ሰላም ኮሚሽን» እንኳን ካለምንም ትግበራ ተስፋችንን ይዞ የሥራ ዘመኑ አብቅቶ እንዲፈርስ ተደርጓል። ከተሰጠው ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ አንጻር መፍትሄ እንደሚያመጣ የታመነበት ቢሆንም የሚጠበቅበትን ሳያደርግ እውቅናውን ተነጥቋል።

በተደጋጋሚ እንዳወራነው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ክስን፣ እርቅን፣ ምህረትን፣ እውነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ካሳን፣ ዴሞክራሲን፣ ፍትህን፤ እንዲሁም፣ መሰል ሁኔታዎችን ያካተተ የፍትህ ሥርዓት ነው። የሽግግር ፍትህ ተግባራዊነት ከሚጠይቃቸው አማራጮች መካከል ታሪካዊ ሁነቶች እንዳሉ ሆነው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አውዶች ከፊት ይሰለፋሉ።

አገራችን በአሁኑ ሰዓት በሽግግር ፍትህ እሳቤ ውስጥ ናት። አሁን ላሉብን ወቅታዊ ችግሮች የትኛውን የሽግግር ፍትህ ስልት ብትጠቀም ይበልጥ ውጤታማ ትሆናለች የሚለው ጥያቄ ለውጤታማነቱ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ነው። ከፍ ብለን እንዳየነው የፍትህ ሥርዓቱ ራሱን የቻለ የትግበራ ሂደት ያለው ነው።

በሽግግር ፍትህ ሂደት ውስጥ ተጠያቂነትን ለማስፈን እውነትን ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ቀዳሚው ርምጃ ነው። እውነትን መሠረት ባደረገ ሂደት ቀጣዩ ክስ ነው። ከዚህ ሂደት በኋላ እንደየአስፈላጊነታቸው እርቅና ምህረት ይከተላሉ። እርቅ ሰዎች ከመለያየትና ከደመኝነት ወጥተው ወደ ቀደመ አንድነታቸው የሚመለሱበት ሂደት ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፈ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ነው ከንድፈ ሀሳብ ባለፈ ተጨባጭ ለውጥ በማምጣት ፍትህን የሚያሰፍነው። አገራችን ኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላምና የወንጀል ተጠያቂነትን ለማስፈን መጀመሪያ በጀመረችው የፍትህ ትግበራ መቀጠል አለባት። ሁለተኛ፣ የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ለውጥ እንዲያመጣ በዓላማና በእቅድ የተመራ የትግበራ እንቅስቃሴ ያስፈልገዋል።

እንደአገር ለሚነሱ ፖለቲካዊም ሆኑ ሌሎች ጥያቄዎች ከመንግሥት ጎን ለጎን ከወገንተኝነት ጸድቶ ምላሽ የሚሰጥ እንደ የሽግግር ፍትህ ዓይነት ገለልተኛ አካል ያስፈልጋል። ይሄ አካል ወደ ማህበረሰቡ ጠልቆ እንዲገባና የምርመራ ሂደቱን እንዲቀጥል ምቹ ሁኔታዎች ያስፈልጉታል።

ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደ መንግሥት እና እንደ ዜጋ በጥያቄና በትብብር መሳተፍ ለውጤቱ ሌላ ተጨማሪ ኃይል የሚፈጥር በመሆኑ አስተዋጽኦው የጎላ ነው። በእውነትና ፍትህ፣ በተጠያቂነትም መርህ የተጎጂዎች ጥያቄ ተመልሶ፤ ወንጀለኞች ፍርድ አግኝተው ሁሉም የእጁን እንዲያገኝ ፈረሱም ሜዳውም እነሆ።

> **ሌላውን ትተን ለአገራችን የመጀመሪያ የሆነውን እና ብዙ ችግሮቻችንን ይቀርፍልናል ስንል እምነት የጣልንበት «የእርቀ ሰላም ኮሚሽን» እንኳን ካለምንም ትግበራ ተስፋችንን ይዞ የሥራ ዘመኑ አብቅቶ እንዲፈርስ ተደርጓል**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

## ዝናብ አጠር አካባቢዎችን ተስፋ ያሰነቀው የበልግ ዝናብ

**ስምስም መንግሥቱ**



የዝናብ ውሃ ስለመያዝ በተገነቡ ግድቦች በዚህ የበልግ ዝናብ በቂ ውሃ መያዝ ተችሏል፤

በልግ የዝናብ ወቅታቸው የነበሩ በርካታ የኢትዮጵያ ክፍሎች በቀደሙት አራት አመታት የዝናብ ጠብታ ጠፍቶ በእጅጉ በድርቅ ተጎድተው እንደነበር ይታወሳል። በእነዚህ አመታት ከፊል አርሶ አደሮች መሬታቸው ጦም አድሮ፣ አርብቶ አደሮችም ለከብቶቻቸው የሚያጠጡት ውሃ አጥተው አይናቸው እያየ ከብቶቻቻውን አጥተዋል፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችንም ለተረጂነት ዳርጓል። ለአራት ተከታታይ አመታት ያጋጠመው የዝናብ እጥረት በተለይም የኦሮሚያ ክልል ቦረና አካባቢ በእጅጉ ለጉዳት መዳረጉን የመገናኛ ብዙኃንም በተከታታይ ሲዘግቡ ቆይቷል።

የበልግ ወቅት በመጣ ቁጥርም የአካባቢው ህዝብ ዝናብ ሲጥል ጠብታ ውሃን እንዲይዝ ለማድረግ ምክረ ሀሳቦች ሲሰጡ ቆይተዋል። ውሃን ለመያዝ የሚያስችሉ የአነስተኛ ግድቦች ግንባታ ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸው አይዘነጋም። የተያዘው የበልግ ወቅትም ከመግባቱ በፊት ጀምሮ በተመሳሳይ ሥራዎች ሲሠሩ ነበር።

በተያዘው የበልግ ወቅት የዝናብ ስርጭቱ የአራቱን አመታት ጉዳት የሚያካክስ በሚመስል መልኩ ሀገሪቱን እያዳረሰ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። የዝናቡ መጠን በዝቷል የሚሉ ወገኖችም ይሰማሉ። አንዳንዶች ስጋታቸውን እንዲህ የሚገልጹት ዝናቡ የሚፈለገውን ያህል ከመጠን ሲያልፍም ጉዳት የሚያስከትል በመሆኑ ነው። የመኸሩ እርሻ በስፋት የሚካሄድበት ወቅትም እየተቃረበ ነው፤ ከሦስት ወራት የክረምት ወቅት በኋላ ደግሞ ሁለተኛ የበልግ ወቅታቸው የሆኑ አካባቢዎች በድጋሚ ይጠብቃሉ።

በዚህ የበልግ ወቅት ስላለው የዝናብ ስርጭትና ለበልጉ የግብርና ሥራ ስላበረከተው አስተዋጽኦ በተለይም ጠብታ ውሃ ሳይቀር እንዲያዝ ይስጥ የነበረው ምክረሃሳብ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆነ፣ውሃውን ለመያዝ የሚያስችሉ አነስተኛ ግድቦችን ለመሥራት የተደረገውን ጥረትና ተግባራዊነቱን፣እንዲሁም የዝናብ ስርጭቱን ቀጣይነት በተመለከተ ዳሰሳ አድርገናል። ትኩረት ያደረግነውም በልግ ተጠቃሚ በሆኑ በኦሮሚያ ክልል የተከናወኑት ሥራዎች ላይ ሲሆን፣ ምክረሃሳብና ወቅታዊውን የአየር ሁኔታ ትንተና መረጃ እየሰጠ ያለውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚትዮሮሎጂ ኤጀንሲ መረጃም አካተናል።

በቅድሚያም የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደሮች ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር ግርማ ረጋሣ በልግ አብቃይ በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች ስላለው የዝናብ ስርጭት ሲያብራሩ እንዳሉት፤ ዝናብ አጠር በሆኑ የክልሉ አካባቢዎች አሁን እየጣለ ያለው ዝናብ ስርጭት ከተጠበቀው በላይ ነው። ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ይገኛል። በተሠሩት አነስተኛ ግድቦችም ውሃ በመያዝ የሚጠበቀውን ግብም ማሳካት ተችሏል።

የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በልግ ወቅታቸው ለሆኑ አካባቢዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ለአነስተኛ ግድብ ሥራ ግንባታ የሚውል በቂ በጀት መድቧል። በዚሁ መሠረትም በክልሉ ቦረናን ጨምሮ ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ከ72 በላይ አነስተኛ ግድቦችን ለመገንባት በእቅድ ተይዞ እየተሠራ ቆይቷል። ከፀጥታ መደፍረስና በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸው ከተስተጓጎለው በአራቱ የወለጋ አካባቢዎች ውስጥ ሊከናወኑ የታቀዱ ስምንት ፕሮጀክቶች እንዲሁም ከምዕራብ ሸዋ፣ደቡብ ምዕራብ ሸዋና ጉጂ አካባቢዎች በስተቀር በአጠቃላይ በክልሉ ሊከናወኑ ከታቀዱት አነስተኛ የግድብ ሥራ ፕሮጀክቶች ውስጥ ወደ 56 ፕሮጀክቶች ተተግብረዋል።

ከነዚህ ውስጥ ወደ 32 የሚሆኑት ፕሮጀክቶች በበልጉ የጣለውን ውሃ ይዘዋል። ከተከናወኑት ፕሮጀክቶች 14ቱ በቦረና ዞን የተሠሩ ሲሆኑ፣ ቀደም ሲል ከነበሩት ግድቦች ጋር ተደምረው በአሁኑ ወቅት በአካባቢው ወደ 18 ግድቦች ይገኛሉ። በግድቦቹ የተያዘው ውሃም ከ20 ሚሊዮን ሜትር ኪዩቢክ በላይ ይገመታል። ውሃው ከአንድ ነጥብ አምስት ኪሎሜትር በላይ የሚተኛ እንደሆነም ኢንጂነር ግርማ ጠቁመዋል።

ግድቦቹ በሀገር በቀል ግብአት በራስ አቅም የተከናወኑ መሆናቸውን የጠቀሱት ኢንጂነር ግርማ ፣ግድቦቹም በዝናብ ወቅት ሊፈጠር የሚችል ጎርፍን ለመያዝ ተብለው የተሠሩ መሆናቸውን ተናግረዋል። በግድቦቹ የተያዘውን ውሃ ለእርሻና ለእንስሳት ብቻ ሳይሆን ሰዎችም አክመው ለመጠጥ ሊያውሉት እንደሚችሉም አስታውቀዋል።

የዝናብ ስርጭቱ የቀጠለ በመሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ በአሁኑ ጊዜ እየተጠቀመ ያለው የዝናብ ውሃ ነው። በተለይም አርብቶ አደሩ እንስሳቱን ይዞ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር በመሆኑ አካባቢው ላይ የማይቆይባቸው አጋጣሚዎች ናቸው ያሉት። ወደ ሌላ አካባቢ ሲሄዱም ወደ ቦታቸው ሲመለሱ ከግድቡ ውሃ ለመጠቀም የሚችሉበት እድል ስለተፈጠረላቸው ስጋቱ ተቃልሏል።

የዝናብ ውሃን ለመያዝ ተብሎ ግድብ መገንባቱ ለተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ልማትም እንዲውል እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት ኢንጂነር ግርማ፣ ለዓሣ እርባታ ልማት እንደሚውልም ነው የገለጹት። በአርብቶ አደሩ አካባቢ በግድብ የተያዘው ውሃ ከመጠን በላይ ሆኖ ሲገኝም በማስተንፈስ አካባቢው ላይ የእርሻ ሥራ የሚከናወንበት ሁኔታ እየተመቻቸ መሆኑም አስረድተዋል።

አሁን እየጣለ ያለው የዝናብ ስርጭት ቀጣይነትና የዝናቡን ውሃ ጥቅም ላይ ለማዋል የተሠሩት ሥራዎች ስላሳደሩት ተስፋና እቅድ በተመለከተም ኢንጂነር ግርማ እንዲህ ሲገልጹ «አርብቶ አደሮች ወደ ግድቡ እንዲሰበሰቡና ወደ ግብርና ሥራውም እንዲገቡ እንዲሁም ተያያዥ የሆኑ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን እንዲሠሩ ያነሳሳሉ። » ሲሉ ሥራዎቹ የኢኮኖሚ ለውጥ ያመጣሉ የሚል እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

የግድብ ፕሮጀክት ሥራ ዓላማው ውሃ መያዝ ብቻ አይደለም፤ ማህበረሰቡን የሚጠቅም ገቢ እንዲያስገኝ መደረግም ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ባለፉት ተከታታይ አራት አመታት ካጋጠመው የዝናብ እጥረት ተሞክሮ በመውሰድና አሁን ያለውን መልካም አጋጣሚ ማዕከል በማድረግ በተለይም በዝናብ እጥረቱ የደረሰውን ጉዳት ለማካካስ የአካባቢው ማህበረሰብን በማነቃቃት እየተሠራ ስላለው ሥራም ኢንጂነር ግርማ ላነሳንላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ «በቆላማ አካባቢ አንዱ ከሌላው ይለያል። ለአብነትም ሐረርጌና ባሌ አካባቢዎች ከፊል አርሶአደር አካባቢ በመሆናቸው የግብርና ሥራ ለመሥራት ፍላጎቱም ተሞክሮውም አላቸው። በሌላኛው ክፍል ደግሞ የእርሻ ሥራ ልምድ የለም። » ሲሉ ይገልጻሉ። «በመሆኑም የንቅናቄ ሥራ ይጠበቃል። ለምሳሌ ቦረና አካባቢ የእርሻ ሥራ ለማከናወን ተስፋ ሰጪ ጀምሮች አሉ። ስልጠናዎችን ለመስጠትና የውይይት መድረኮችንም ለማዘጋጀት ሥራዎች ተጀምረዋል። ማህበረሰቡ ከደረሰበት የከፋ ችግር ትምህርት በማግኘቱ ግንዛቤው ተቀይሯል ሲሉም ነው ያብራሩት።

እንደ ኢንጂነር ግርማ ማብራሪያ፤ በክልሉ በአራት አመታት ውስጥ ወደ 255 ግድቦች ለመሥራት እቅድ ተይዞ ተያያዥ የሆኑ ተጨማሪ ሥራዎችን በመሥራት አካባቢዎቹ ላይ ለውጥ ለማምጣት እየተሠራ መሆኑን ነው። የበልጉ ወቅት እስከ ግንቦት 30 የሚቀጥል በመሆኑ ስርጭቱ ከመጠን በላይ ይሆናል የሚለው ጉዳይ ስጋት አይደለም፤ ግድቡ 20 ሜትር ከፍታ አለው። ይህ እስኪሞላ ድረስ መጠበቅ የሚቻልበት እድል አለ። ቢሞላም ማስተንፈሻ የተሠራለት በመሆኑ በዚህም መንገድም ማስተንፈስ ይቻላል።

ዝናቡ የሚቋረጥበት ሁኔታ ቢያጋጥም በግድቡ የተያዘውን ውሃ ለተወሰነ አመት ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑም አመልክተዋል። ውሃ በባህሪው በትነትና በአጠቃቀም ጥንቃቄ ጉድለት የሚቀንስ መሆኑን ግምት ውስጥ መግባት አለበት ብለዋል።

ከመስከረም ወር በኋላ የሚከተለው ሁለተኛው የበልግ ወቅት ተስፋ የተጣለበት መሆኑን በመጥቀስ በዚያን ጊዜም በተመሳሳይ የዝናብ ስርጭቱ ጥሩ ከሆነ ስጋቶች እንደሚቀንሱም ተናግረዋል። መስሪያ ቤታቸው ከኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ጋርም ጥሩ ግንኙነት እንዳለው ጠቅሰው፣ ኢንስቲትዩቱ በሚሰጠው የመረጃ ትንተና መሠረት እንደሚሠራም ገልጸዋል።

በዚህ የበልግ ወቅት ስለተከናወኑት ተግባራትና ወቅታዊውን የዝናብ ስርጭት በተመለከተ ያነጋገርናቸው የኢትዮጵያ ሚትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ሚትዮሮሎጂ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሳምነው ተሾመ እንዳሉት፤ በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑ የኢትዮጵያ ክፍሎች በተለይም በድርቅ ተጽእኖ ሥር በነበሩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለአብነትም ሶማሌ፣ ጉጂ፣ቦረና፣ የተወሰኑ የሲዳማ ክልል፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ህዝቦች አካባቢዎች ከየካቲት 30ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለበልግ አመቺ የሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ተፈጥረዋል። በአብዛኞቹ አካባቢዎችም የዝናብ ስርጭት መኖሩን ከተሰበሰቡ የሚትዮሮሎጂ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል።

በ24 ሰዓት ውስጥ በአንድ የሜትዮሮሎጂ ጣቢያ ላይ ከአንድ ሚሊ ሊትር እስከ አስር ሚሊ ሊትር መጠን ያለው ዝናብ በሚጥልበት ጊዜ ዝናቡ ቀላል የዝናብ መጠን ያለው ተብሎ ሊጠራ ይችላል፤ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ11 ሚሊ ሊትር እስከ 29 ሚሊ ሊትር መጠን ያለው ዝናብ ከጣለ ደግሞ ዝናቡ መካከለኛ፣በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚሊ ሊትር በላይ ያለው መጠን ዝናብ ከጣለ ደግሞ ዝናቡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተብሎ ይጠራል።

ከየካቲት 17 ቀን 2015ዓ.ም ጀምሮ በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነው የሀገሪቱ አካባቢዎች ከቀላል እስከ ከመካከለኛ፣ በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ስለመጣሉ በሚትዮሮሎጂ ጣቢያዎች መመዝገቡን አስረድተዋል።

በአጠቃላይ ከየካቲት 17 እስከ ሚያዝያ 23 ቀን 2015 ዓ.ም 77 በሚደርሱ የሚትዮሮሎጂ ጣቢያዎች ከባድ መጠን ያለው (ከ30 እስከ 160 ሚሊ ሊትር) ዝናብ ተመዝግቧል ያሉት ዶክተር አሳምነው፣ በአጠቃላይ በተጠቀሱት ቀናት በልግ ዋነኛና ሁለተኛ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተስፋፋና የተጠናከረ የዝናብ ሁኔታ ነበራቸው ብለዋል። በዚህም ግብርና ሥራን ከማሳለጥ፣ ልምላሜን በመጨመር፣ ድርቁን ከማስታገስ፣ እንዲሁም ግድቦች በቂ ውሃ እንዲይዙ በማስቻል፣ በተፋሰሶችና በወንዞች ለነበረው የውሃ አቅርቦትም ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን አስታውቀዋል።

የኢንስቲትዩቱን የትንበያ መረጃና ምክረሀሳብ መሠረት በማድረግ በዝናብ የተገኘውን ውሃም በመሰብሰብ ረገድ በማህበረሰቡ በኩል እየተደረገ ያለውን ጥረት ኢንስቲትዩቱ በተለያየ መንገድ ከሚያገኘው መረጃ በመገንዘብ እንዲህ ያሉ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው ታምኖባቸዋል።

ዝናቡ በዝቷል ተብሎ እንደ ስጋት ለሚነሳውም ስጋቱ አንጻራዊ ሊሆን እንደሚችል በመጠቆም ስጋቱ የመጣው ቀደም ባሉት አምስት የበልግ ተከታታይ ወቅቶች ከመደበኛ በታች ከነበረው ዝናብ ጋር ተያይዞ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል። ከአመታዊ የዝናብ መጠን እስከ 55 በመቶ የሚሆነው የዝናብ መጠን የሚገኘው በበልግ ወቅት እንደሆነም አመልክተዋል።


በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆነው ሶማሌ፣ ደቡብ ኦሮሚያ ቆላማ ስፍራዎች፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ሲዳማ፣ የደቡብ ብሔርና ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ መደበኛ የሆነ ዝናብ እንደሚኖራቸውና የዝናቡም አገባብ ሊዘገይ እንደሚችል ቀደም ሲል ትንበያ መስጠቱ ይታወሳል።

የበልግ ዝናብ ሁለተኛ ወቅታቸው የሆኑ ደቡብ ትግራይ፣ ምሥራቅ አማራ፣ አፋር፤ ሐረርና ድሬዳዋን ጨምሮ መካከለኛ የሀገሪቱ አካባቢዎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚኖራቸውና መዘግየትም እንደሚኖር ኢንስቲትዩቱ በተጨማሪ ትንበያ ሰጥቶ ነበር። በቅድመ ትንበያው መሠረትም የበልግ ዝናብ ከየካቲት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በተለያየ መጠን በመጣል ላይ ይገኛል። በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎችም የደመና ሽፋኑ ጨምሯል። አካባቢዎቹ ከቀላል እስከ ከባድ የዝናብ መጠን አግኝተዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ በደረሱ ሰብሎች፣ እንስሳትና በሰው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል።

ኢንስቲትዩቱ ባለፈው ጥር ወር 2015 በጀት አመት ላይ በበጀት አመቱ ስለሚኖረው የአየር ትንበያ ሁኔታ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ መድረክ አዘጋጅቶ የሚጠበቀውን የአየር ሁኔታ ይፋ ማድረጉም ይታወሳል።

# ብሔራዊ የቅድመ ልጅነት ፖሊሲ ማዕቀፍ ትግበራ ለተሻለ ዕድገት

**ሰላማዊት ውቤ**



የቅድመ ልጅነት በሰው ልጆች የሕይወት ዑደት ውስጥ በቀጣይ የሕይወት ዘመን ብሩህና አምራች ዜጋን ከማፍራት አንፃር ወሳኝነት አለው። ሳይንሱ እንደሚያመላክተው በተለይ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ወሳኝና አእምሮ ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት የሚያድግበት ነው። ታዲያ በዚህ ፈጣን የዕድገት ለውጥ የተሻለ ምግብ፣ የጤና አገልግሎት፣ ሁለንተናዊ እንክብካቤና የትምህርት ዕድል መስጠት አስፈላጊ እንደሆነም ሳይንሱ ይጠቁማል። ይሄ ለአንድ አገር ሁለንተናዊ ዕድገትም ሆነ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት መስፈን የራሱ አስተዋጽኦ እንዳለውም ይጠቀሳል።

ይሁንና በቅድመ ልጅነት ዘመን የሚሠራው ሥራ ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር እንደ ግለሰብ ጀምሮ እንደ አገር የጎላ ጉዳት ያስከትላል። በተለይ በትምህርቱ ዘርፍ የሚያሳድረው ጫና ከፍተኛ ነው። ለአብነት ከጠቅላላው ሕፃናት 55 በመቶው የትምህርት ዕድልን አለማግኘታቸው ተጠቃሽ ነው። ሩቅ ሳንሄድ ባሳለፍነው ዓመት የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ከወሰዱት ተማሪዎች ውስጥ የማለፊያ ነጥብ አግኝተው ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባት የቻሉት ሦስት በመቶ ብቻ መሆናቸውም ሌላው ማሳያ ነው።

ባሳለፍነው ሳምንት መጨረሻ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ይሄን ታሳቢ በማድረግ ብሔራዊ የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ መርሐ ግብርን በሂልተን ሆቴል ይፋ አድርጎ የነበረ ቢሆንም የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድ ገትና ትምህርት በአገራችን በፖሊሲ ማዕቀፍ ደረጃ ትኩረት አግኝቶ የተጀመረው በ2005 ዓ.ም ነው። ይሄን መሠረት አድርጎም በቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ረገድ ሁለንተናዊ የሕፃናት እንክብካቤ በጤና፣ በትምህርትና ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። ለአብነትም ልጆች ደህንነቱ በተጠበቀ ምቹ አካባቢ እንዲኖሩ፣ በቂና የተመጣጠነ ምግብ በተጨማሪም ቀዳሚ ማነቃቃቶችና የቅድመ አንደኛ ወይም መደበኛ ክፍል ትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ማድረግ ሲሠሩ ከነበሩት ሥራዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

ታዲያ በመድረኩ መክፈቻ ላይ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ስለ ቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ፋይዳ ‹‹በልጆች ዕድገትና ትምህርት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ ፋይዳን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል›› ሲሉ ገልፀውት ነበር።

እንዳሉት በልጆች ዕድገትና ትምህርት ላይ ሙዓለ ንዋይ ማፍሰስ ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ልማትና ማህበራዊ ፋይዳን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይጫወታል። ይህ የሙዓለ ንዋይ ፍሰት በልጆች ሁለንተናዊ ዕድገት የሚደረገውን ጥረት ያማከለና ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት። የልጅነት ዕድገትና እንክብካቤ ከጨቅላነት ጀምሮ አቀራረቡን ሁለንተናዊ በማድረግ ከልጆች ማህበራዊ፣ አካላዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ደህንነት እንዲሁም የመማር ዕውቀት ገጽታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ መንግሥት ሲቪል ማህበራት ወላጆች፣ ለጋሾችና ማህበረሰቡ በትብብር ሲሠሩ ነው። እንዲህ ዓይነት ጥረቶች ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈውን የድህነት አዙሪት በማቋረጥ ሂደት ውስጥ የጎላ ድርሻ አላቸው። ለሁለንተናዊ የአገር ብልጽግናም መሠረት ይጥላሉ። ሁለንተናዊ የሕፃናት ልማት በሚተገበርበት ወቅት ትምህርት በቅንጅት ሥራና ግንዛቤን በመፍጠር ረገድ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት የተገነዘበው የኢፌዴሪ መንግሥት ለቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል ብለዋል።

**‹‹የሕፃናት ሁለንተናዊ ልማት በአገሪቱ አጠቃላይ የሰው ሀብት ልማት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው››**

ለዚህም መንግሥት ቀጣይነት ያለው ልማት እንዲኖር ቅድሚያ ለሕፃናት በመስጠት ኢንቨስት እያደረገ እንደሚገኝ አንስተዋል። በልጆች ላይ የሚሠሩ ሁሉም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በተቀናጀ መልኩ መሥራት እንዳለባቸውም አሳስበዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ቃል ከገባው አንዱ የጤና መታወክ ተጋላጭ ለሆኑ በዝቅተኛ የጥራት ደረጃ የሚገኘውን የቅድመ ትምህርትና የማህበራዊ ችግሮችን በማቃለል ለሁሉም ሕፃናት ድጋፍና ዕድል በመስጠት የሕፃናትን ፍላጎት ማሟላት ነውም ብለዋል። ሁለንተናዊ ሕፃናት ዕድገት ውስጥ ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ትምህርት ሚኒስቴር

> **ይሁንና በቅድመ ልጅነት ዘመን የሚሠራው ሥራ ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር እንደ ግለሰብ ጀምሮ እንደ አገር የጎላ ጉዳት ያስከትላል። በተለይ በትምህርቱ ዘርፍ የሚያሳድረው ጫና ከፍተኛ ነው። ለአብነት ከጠቅላላው ሕፃናት 55 በመቶው የትምህርት ዕድልን አለማግኘታቸው ተጠቃሽ ነው**

የተሻለ የትምህርት አካባቢ በመገንባትና የተለያዩ ባለ ድርሻ አካላት ትኩረታቸው ጥረቶችን በማስተባበር ሁሉንም ተሳታፊ በማድረግ በዘርፉ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በተሻሻለው የፖሊሲ ማዕቀፍ እያንዳንዱ ልጅ ወደፊት አምራች ዜጋ እንዲሆን በሚደረገው ሂደት ትምህርት ሚኒስቴር ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ወላጆች፣ ማህበረሰቦች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የልማት አጋሮችና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ቅድመ ትምህርትን ለማሻሻል የቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገትና ትምህርት አገልግሎት በመስጠት ረገድ የሚጫወቱትን ሚና በግልጽ የሚረዳ መሆኑንም አውስተዋል። በቅድመ ልጅነት ዘመን ዕድገት በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሦስት በመቀጠልም በመጀመሪያዎቹ ሰባት ዓመታት የሚደረግ እንክብካቤና ጥበቃ ለሕፃናት ጤናማ ዕድገትና ለቀጣይ የሕይወት ዘመናቸው መሠረት የሚጥል በመሆኑ እጅግ ወሳኝ ነውም ብለዋል።

በዚሁ መድረክ በጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ የተወከሉት ዶክተር መሠረት ዘለዓለም እንዳሉትም በቅድመ ልጅነት ዘመን ለሕፃናት ጥሩ የጤና አገልግሎት በቂና የተመጣጠነ ምግብ፣ ደህንነትና ጥበቃ፣ ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ፣ ቀዳሚ ማነቃቃትና የቅድመ መደበኛ ትምህርት ዕድል አለማቅረብ ሕፃናት በቀጣይ ሕይወት ምርታማ ዜጋ እንዳይሆኑ እንደሚያደርግ ተናግረዋል። እንደ ተወካይዋ የተሻለ ሕይወት የመምራት ዕድላቸውን ያሰናክላል። የተለያዩ ጥናቶች የሚያመላክቱትን ዋቢ አድርገው እንደተናገሩት፣ የቅድመ ልጅነት ዕድገትና መዳበር ላይ መሥራት እንዲሁም የሕፃናትን ጤና መጠበቅ በአካል፣ በአእምሮ በማህበራዊ ኑሮና በስሜት ክዋኔያቸው በዕድሜያቸው ሊደርሱበት በሚችሉት የላቀ የመዳበር ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል። ወደፊት ለሚኖራቸው ስኬታማ ሕይወትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለአገር መረጋጋት፣ የላቀ ዕድገትና ልማትም ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አለው። ቅድመ ልጅነት ላይ የታለሙ መርሐ ግብሮችን መተግበር የሰው ኃይል ካፒታል የመመለስ ትልቅ አቅም አላቸው። የቅድመ ልጅነት ዕድገት መዳበርና ትምህርት ፖሊሲ ማዕቀፍ ከጽንስ እስከ ሰባት ዓመት ዕድሜ ክልል ለሚገኙ ሕፃናትና ወላጆቻቸው ወይም ተንከባካቢዎቻቸው የሚሰጡ አገልግሎቶችን የሚያመላክት ሁሉን አቀፍ ፖሊሲና መርሐ ግብር አካቷል። በመሆኑም ሊተገበር የሚችልና አዋጭ እንዲሆን የፖሊሲው መተግበር የአገራችን ሕፃናት የተሻለና ጤናማ ሕይወት ጅማሬ እንዲኖራቸው አንድ እርምጃ ለመራመድ ያስችላል።

ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ኃላፊነት የሚሰማቸውና ምርታማ ዜጋ እንዲሆኑ ያግዛል። በድምሩ በቅድመ ልጅነት ዘመን ያለውን የአመጋገብ፣ የጤና፣ ደህንነትና ጥበቃ ምላሽ ሰጪ የተለያዩ ዘርፍ ተቋማትን ድጋፍ በብርቱ ይፈልጋል። የቅድመ ልጅነት ዘመን ያለውን የአመጋገብ፣ የጤና ደህንነትና ጥበቃ ምላሽ ሰጪ እንክብካቤ ቀዳሚ ማነቃቃትና የቅድመ መደበኛ ትምህርት አገልግሎት ማዳረስና ማሻሻል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ማስገኘቱንም ገልፀዋል።

83 በመቶው የአገራችን ሕዝብ በገጠር መኖሩን ያወሱት ዶክተር መሠረት ‹‹ሁሉም ሕፃናት ተመሳሳይ ፍላጎት አላቸው ብዬ አስባለሁ›› በቅድመ ልጅነት ፖሊሲ ማዕቀፍ ትግበራው ገጠር የሚኖሩ ሕፃናት ተጠቃሚ መሆን አለባቸውም ብለዋል። በተለይም በአርሶ አደሩና በአርብቶ አደሩ ዘንድ ሥራው መስፋፋትና ወላጆችም ትግበራውን በዘላቂነት ማስቀጠል እንዳለባቸውም አመልክተዋል። እንዲህ ሲባል ከተሞች ላይ ያሉ ሕፃናት ተጠቃሚ መሆን የለባቸውም ማለት አይደለም። ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ያሉ ሕፃናት የግድ የትግበራው ተጠቃሚ መሆን አለባቸው። ሁለንተናዊ ፍትሐዊነትን ማረጋገጥም አስፈላጊ ነው። ትምህርት፣ ጤና፣ ስነ ምግብ፣ የአካባቢ ደህንነት፣ አጠቃላይ ሁለንተናዊ ሁኔታቸው መጠበቅና ሕፃናት የቅድመ ልጅነት ዘመናቸውን እነዚህ በተሟሉበት ሁኔታ እንዲያሳልፉ ማድረግ ለአገር ዕድገትም ሆነ ከድህነት ለመውጣት ያስችላል ሲሉ ገልጸዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትሯ ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በተወካያቸው በኩል ባስተላለፉት መልዕክትም በአገራችን በሕፃናት ዕድገት ዙሪያ የተሻሉ ለውጦች እየተመዘገቡ ነው። ይሁንና አሁንም ገና ምላሽ ያላገኙ በርካታ ጉዳዮች አሉ። ለአብነት በተለይ በሕፃናት አስተዳደግ ዙሪያ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን፣ በሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ማሳያ ናቸው። በአገራችን በዕድገት ደረጃቸው ለሕፃናት ሊሰጡ የሚገቡ የቅድመ ልጅነት አገልግሎቶች አለመስፋፋታቸውም ሌላው ነው። ሦስተኛው ለልጆች ምቹና ተስማሚ መኖሪያ ለመፍጠር ያለመቻል፣ በዚህ ላይ የተጠናከረ የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓትም መጓደል፣ በነዚህና ሌሎች በርካታ እጥረቶች ምክንያት የቅድመ ልጅነት ዘመን ውስጥ የሚገኙ ሕፃናት ተገቢው አያያዝ አልተደረገላቸውም። ባለተመቻቸ ሁኔታ የሚገኙ ናቸው። በዚህም ምክንያት ለተለያዩ ችግሮችና ጥቃቶች ለመጋለጥ ተዳርገዋል። መንግሥት በ2009 ዓ.ም ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው ብሔራዊ የሕፃናት ፖሊሲ መሠረት የሕፃናት መብትና ደህንነት በማክበር፣ በማስከበርና ፍላጎታቸውን በማሟላት ረገድ እየወሰደው ያለው እርምጃ ይበልጥ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ በሕፃናት መልካም አስተዳደግና ስብዕና ግንባታ፣ የቤተሰብ፣ የማህበረሰብና የመንግሥትን ሚና ለማሳደግ ተችሏል። ፖሊሲው የአገራችን ሕፃናት የቅድመ ልጅነት ዘመናቸውን በአግባቡ የሚያሳልፉበት ሁኔታ ለማመቻቸት መልካም ስብዕና የተላበሰ ዜጋ ማፍራት ይቻል ዘንድ የተቀናጀ ጥረትና ድጋፍ በተሻሉ የሕፃናት አስተዳደግ ዘዴዎች የቤተሰብ ተንከባካቢዎችና መምህራን ክህሎት ማሳደግ፣ የማህበረሰቡን ሚና ማሳደግ፣ የማህበረሰቡን ሚና ማጎልበት፣ ምቹና ተስማማሚ አካባቢን መፍጠር፣ የሕፃናት ጥበቃ ሥርዓት ማጠናከር ፣ ለሕፃናት መልካም ዕድገት አስተዋጽኦ ያላቸው አገልግሎቶቹን ማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቷቸው መከናወን እንዳለባቸው አሳስበዋል።

የኢማጅን ዋን ደይ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ማናጀር የሆነችው ወጣት ሀዊ ዓለሙ እንደተናገረችው፣ ድርጅቷ በ2030 ሁሉም ሕፃናት ከውጭ ድጋፍ ነፃ የሆነ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ የማድረግ ጥረቱን ከጀመረ ዘንድሮ 16 ዓመቱን ይዟል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሥራውን የጀመረበትን ትግራይ ጨምሮ በስድስት የአገራችን ክልሎች በተለይ በአርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ልጆች ዙሪያ ብዙ ሠርተዋል። ከሥራቸው ዋናው በነዚህ በአርብቶና አርሶ አደር አካባቢ ያሉ ትምህርት ቤቶችና የማህበረሰብ ክፍሎች ዘላቂ የኢኮኖሚ አቅም እንዲኖራቸውና የልጅ አስተዳደግና አያያዝ አመለካከታቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ከገቡበት ክልል ዘላቂ የሆነ ለውጥ ሳያመጡ በፍፁም አይወጡም። በተለይ እነኝህን ሁለት ሁኔታዎች አሟልቶ መውጣት የኢማጅን ዋን ዴይ መርህ ነው። ትምህርት ቤቶችን ከመገንባት ጀምሮ በቁሳቁስ እስከማሟላትና የአካባቢውንና የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ አቅም እስከማጎልበት የሚሠሩት ሥራ ሦስት ዓመት እንደሚፈጅባቸውም ወጣቷ ነግራናለች። በዚህ አሠራር 946 ትምህርት ቤቶችን ተደራሽ ማድረግ ችለዋል። ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥም 123ቱን የገነባቸው ድርጅቱ ነው። በዚህም ከ175 ሺህ በላይ የትምህርት ቤት ደጃፍ ረግጠው የማያውቁ ሕፃናት የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ማድረጉን ታነሳለች። ከ453 ሺ በላይ የሚሆኑ ሕፃናትን የሕፃናት ጥበቃና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ማድረጉንም ታወሳለች። ትምህርት ቤቶችንና ትምህርት ቤቶች አካባቢ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የንፁህ ውሃና የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ሕፃናት የቅድመ ልጅነት ዘመናቸውን በተመቻቸ ሁኔታና ሥፍራ እንዲያሳልፉ አድርገዋል።

በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ፕሮግራሞችና ጥራት መሻሻል መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዮሐንስ ወጋሶ እንደሚሉት ከተሻሻለው ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ አንፃር የቅድመ ልጅነት ዘመን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው መቻሉን ያነሳሉ። ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ በትምህርት ባለድርሻዎችና በሌሎች ቅንጅት እንዲተገበር መደረጉንም በማሳያነት ያወሳሉ። ይሄንና ሁሉንም ሕፃናት ተደራሽ አላደረገም ነበር። 55 በመቶው ሕፃናት የመማር ዕድል ሳያገኙ መቅረታቸውም ሌላው ነው።

‹‹ወላጆች በቂ ግንዛቤ ኖሮን ጤናቸውን ጠብቀን አንልክም፣ የምንሰጠውም የትምህርት አገልግሎት ውጤታማ አልነበረም›› ያሉት ኃላፊው የፖሊሲ ማዕቀፉ እነዚህን መሠረታዊ ችግሮች ሊፈታ በሚችል መልኩ የተቀመጠ መሆኑን ያወሳሉ። እንደሳቸው ፖሊሲ ማዕቀፉ ወደ ቅንጅታዊ ትግበራ ሲገባ ልጆች ጤንነታቸው ተጠብቆ ምግብ በአግባቡ አግኝተው ያደርጋሉ። ይሄን ካገኙ አስተሳሰባቸው የተሻለ ይሆናል። በዚህ ልክ የመጡ ሕፃናት ዕድሜያቸው አራት ዓመት ሲሆን ጥራት ያለው ትምህርት ቤት ውስጥ ይገቡና አገልግሎቱን ያገኛሉ። ወደ ቤት በሚመለሱበት ጊዜ ደህንነታቸው ይጠበቃል። የትምህርት ጥራት የመሻሻሉም በጣም ከፍተኛ ይሆናል። ትምህርት ቤቶች ምቹ ሳቢና ማራኪ እንዲሆኑ ለማስቻል የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ ፕሮግራም በቅርቡ ይፋ ይሆናል።

እኛም ሁሉም አካላት በዚህ መልክ ተቀናጅተው በቅድመ ልጅነት ዘመን ላይ ቢሠሩ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ተነቃቅተው ይመጣሉ፣ በአግባቡ ይመገቡና ጤናቸው ይጠበቃል፣ እንደ አገር ያሰብንበትም በመድረስ እድገታችንን በዘላቂነት መሥራት እንችላለን በማለት ጽሑፋችንን ቋጨኝ።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹መመሪያው የሰበር ውሳኔዎች አጠቃሳይ ሒደት ግልፅ እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያግዝ ነው››

**አቶ አሮን ደጎል**
**በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምርምር እና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክተር**

ምሕረት ሞገስ

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም ውሳኔዎች ለማረም በሰበር የማየት ስልጣን ተሰጥቶታል። የሰበር ችሎቱ የሚመራበትን ሥነሥርዓት በሕግ የመደንገግ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረት በሚያዝያ 2015 የሰበር ሥነሥርዓት ሕግ አውጥቷል። ተፈፃሚ መሆን የጀመረው በሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ነው። ይህ የሥነሥርዓት ሕግ ለምን እስከ አሁን ዘገየ? ይዘቱ ምንድን ነው? በሚሉት ጉዳዮች ላይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምርምር እና ሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አሮን ደጎልን በማነጋገር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**


ፎቶ -ገበበ ገብሬ

**አዲስ ዘመን፡- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማናቸውንም የሰበር ውሳኔዎች የማየት ሥልጣን አለው ሲባል ምን ማለት ነው?**

**አቶ አሮን፡-** በ1987 ዓ.ም የፀደቀው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 80 ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን በተለይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ሥልጣን ያስቀምጣል። ውሳኔዎች እና የሕግ አተረጓጎሞች ወጥ እንዲሆኑ ለማድረግ በሚያግዝ መልኩ በአገሪቱ በማናቸውም አካል በተሠጠ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ብሎ ካመነ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት፤ አይቶ የመዳኘት ሥልጣን እንዳለው አስቀምጧል።

የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የፌዴራላዊ ሥርዓቱን ተከትሎ በክልል እና በፌዴራል ተከፋፍሏል። ሌሎች አገራት ለምሳሌ ሕንድ ፌዴራላዊ ሥርዓትን የምትከተል አገር ናት። ፍርድ ቤቶቿ ግን ማዕከላዊ ናቸው። ነገር ግን እንደአሜሪካን ያሉ ሌሎች የፌዴራል አገራት በመሆናቸው ሕግ አውጪውም፣ ሕግ ተርጓሚውም ሆነ ሕግ አስፈፃሚውም ፍርድ ቤቶችም አደረጃጀታቸው ፌዴራላዊ ነው።

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋነኛነት የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ያለው ነው። የፍትሐብሔር ጉዳይ የሚጀምረው ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። የወንጀል ጉዳዮችም ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚጀምሩ ናቸው። ከፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚጀምሩ አሉ። እንደየወንጀሉ ውስብስብነት ማለት ነው። የፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ የሚያያቸው ጉዳዮች አሉ። በፍትሐ ብሔር እና በይግባኝ የሚያያቸው ጉዳዮች አሉ። በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ በይግባኝ ወደ የፌዴራል ከፍተኛ ደረጃ ፍርድ ቤት ይመጣል።

ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስንመጣ በዋናነት በይግባኝ እና በሰበር የሚመጡ ጉዳዮችን ይመለከታል። በእርግጥ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ የሚያየው አንድ ጉዳይ ክስን ስለማዘዋወር ነው። አንድ ጉዳይ ወይም አንድ መዝገብ ከአንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ፍርድ ቤት ይዘዋወርልኝ የሚል ጥያቄ ሲነሳ ወይም ከአንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም ክሱ ይዘዋወርልኝ የሚል ጥያቄ ሲነሳ ያዘዋውራል። ወይም ወደ ራሱ እንዲዘዋወር ያደርጋል። የመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ይህ ብቻ ነው። ከዚህ ውጪ ያለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ እና የሰበር ሥልጣን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሰበር ስንል በራሱ ምን ማለታችን ነው?**

**አቶ አሮን፡-** ሰበር ስንል መስበር ማለት ነው። የሚሰበረው ከስር ጀምሮ የመጡት ውሳኔዎች መሠረት ያደረጉት የሕግ ድጋፍ ወይም መሠረት ሲተረጎም በትክክል አልተተረጎመም። ሰፋ ባለ መልኩ መተርጎም ሲገባው ጠቦ ተተርጉሟል። ጠበብ ተብሎ መተርጎም ሲገባው አላግባብ ሰፍቷል ሲባል፤ እንዲሁም የባለጉዳዩን መብት በሚያጣብብ እና ሰብአዊ መብትን በሚነካ መልኩ ተተርጉሟል ስለዚህ መስተካከል አለበት ብሎ ካመነ አስገዳጅ በሆነ መልኩ የሕግ ትርጉም ይሠጣል።

በዋናነት ሐሳቡ በኢትዮጵያ ሲታይ ፌዴራላዊ የሰበር ሰሚ አንድ ችሎት ናት። ለምሳሌ የሰበር አጣሪ የምንለው ሦስት ዳኞች ተሰይመው የሚያስችሉበት አለ። በዚህ በአዲሱ መመሪያ ይህ አጣሪ ችሎት ሕጋዊ ድጋፍ አግኝቷል። ዋናው ደግሞ ሰበር ችሎት አለ። በዚህ ላይ አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ነው። በፈረንሳይ ግን ሰበር ራሱን የቻለ ችሎት ነው። ፈረንሳይ በእርግጥ ዩኒተሪ (ማዕከላዊ) ናት፤ የሰበር ፍርድ ቤቱ በጣም ትኩረት ተሰጥቶት፤ በሁሉም ፍርድ ቤቶች እንደሕግ ሊጠቀስ የሚችል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሰበሩ ውሳኔ እንደሕግ ይቆጠራል ማለት ነው?**

**አቶ አሮን፡-** በትክክል፤ በውሳኔም ሆነ በክርክር ወቅት በአንቀፅ ይህ ንዑስ ቁጥር ይህ እና በሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር ይህ በዚህ በዚህ ቀን በተላለፈው ውሳኔ መሠረት እያልን እንደሕግ እንጠቅሰዋለን። ይህ አስገዳጅነት ስላለው ማለት ነው። ይህን ያህል አስፈላጊ ሆኖ ሳለ፤ እስከ አሁን በግልፅ የሚመራበት ሥርዓት አልነበረውም። የሰበር ጉዳዮች ሲመጡ ዳኞቻችን መደበኛውን የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግን ይጠቀሙ ነበር። ይህ ደግሞ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል።

ምክንያቱም የሰበር ሰሚ ዳኞች መደበኛውን የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ሥነሥርዓት ሕግን ይጠቀሙ ነበር። ይህ ደግሞ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል። ምክንያቱም የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንደኛ በራሱ ይዘቶቹ በርካታ ሊስተካከሉ እና ሊሻሻሉ የሚገቡ አሁን ኢትዮጵያ ከያዘችው የፌዴራል ሥርዓት አንፃር ሊቃኙ የሚገባቸው በርካታ ድንጋጌዎች አሉ። የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ለመደበኛ ክርክር ተብለው የተቀመጡ ናቸው። የወንጀል ሥነሥርዓትም እንደዚያው ነው።

የፍትሐ ብሔር ሥነሥርዓት ሕግ በ1958 ዓ.ም የፀደቀ ነው። ከ60 ዓመት በላይ ሊሆነው ነው የወንጀል ሥነሥርዓት ሕግም 1954 ዓ.ም የፀደቀ ነው። ይህም በርካታ ዓመታትን አልፏል። ያኔ በንጉሡ ዘመን ኢትዮጵያ የምትከተለው አሃዳዊ ሥርዓትን ነበር። ስለዚህ እነኚህ የሥነሥርዓት ሕጎች ከጊዜው ጋር መሔድ አለባቸው። በራሳቸው ከሰበር ጋር ባይያያዙም በርካታ ሊሻሻሉላቸው የሚገቡ ድንጋጌዎች አሏቸው።

የወንጀል የሥነሥርዓት ሕግ ፓርላማ ቀርቦ ጫፍ ደርሷል ማለት ይቻላል። የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ግን የማሻሻያ ሒደት ገና አልተጀመረም። ጊዜውን የሚመጥኑ ናቸው ቢባል እንኳ ለሰበር በሚያመች መልኩ የተቀመጡ አይደሉም። በእርግጥ በንጉሡ ነገስቱ ዘመንም ዙፋን ችሎት የሚባል ነበር። ዙፋን ችሎት ከሰበር ጋር ትንሽ የመመሳሰል ነገሮች አሉት። ነገር ግን እነኚህን የሥነሥርዓት ሕጎችን ተጠቅሞ ለሰበር ውሳኔ መሠረት ማድረግ ያስቸግራል።

የሰበር ባህሪ የተለየ ነው። ለምሳሌ በመጀመሪያ ደረጃ እና በይግባኝ ክርክር ወቅት የፍሬ ነገር ክርክርም ሆነ የሕግ ክርክር ይቀርባል። ፍርድ ቤቱ በፍሬ ነገሮችም ውሳኔ ይሠጣል፤ በሕግ ጉዳዮችም ውሳኔ ይሰጣል። ለምሳሌ ተዋዋይ ወገኖች ቢኖሩ አንዱ ውል አለ ሲል ሌላው ውል የለም ይላል። ይህ እውነታ (ፋክት) ሲሆን በማስረጃ ይቀርባል። የተሻለ ማስረጃ ያቀረበ እና ዳኛውን ያሳመነ ውሳኔ ያገኛል። ወደ ሰበር ሲመጣ ግን እውነታዎች አይታዩም። በእስር ፍርድ ቤት ያለቀ ነው። እዚህ የሚመጣው የእስር ፍርድ ቤቱ ላይ እውነታውን እና ማስረጃውን መዝነው ለዚህ ውሳኔያቸው መሠረት ያደረጉት ዋነኛ የሕግ ድንጋጌ ላይ ሲተረጉሙት ተሳስተዋል። ይህ ስህተት ደግሞ ተራ ሳይሆን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ይሉታል።

**አዲስ ዘመን፡- መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው?**

**አቶ አሮን፡-** በአዲሱ አዋጅ 1234/2013 ላይ በግልፅ አስቀምጦታል። ይህ በአዋጅ 1234/2013 ዓ.ም የወጣ ሲሆን፣ ብዙ ማሻሻያዎችን የያዘ ነው። የተለያዩ ክፍተቶች ያሉበት ነው። አሁን ወደ ማሻሻል ለመሔድ እየተንደረደርን ነው። ነገር ግን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ለብዙ ጊዜ ሲያከራክር የነበረ ነው። ሰበር ማናቸውንም በስር ፍርድ ቤት የተወሰኑ ውሳኔዎችን በተመለከተ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ካለባቸው ያያል ቢልም፤ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው አከራካሪ ነበር።

በቅርቡ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 በአንቀፅ 2 ላይ ንዑስ ቁጥር 4 ላይ ትርጉም ሰጥቶበታል። ‹‹መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት ያለበትን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10 መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ የመጨረሻ ውሳኔ ፍርድ ብይን ትዕዛዝ ማለት ነው›› ይላል።

ስለዚህ መሠረታዊ መብትን የሚነኩ ሕገ-መንግሥታዊ መብትን የሚጥሱ ለምሳሌ በሕገ-መንግሥቱ እንደተቀመጠው ፍትህ የማግኘት መብት ሕገ-መንግሥታዊ ነው። ፍትህ ቢከለከል መዝገብህን አናይም ቢባል ይህ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው። ከዚያም በመለስ ደግሞ ዘርዝሯቸዋል። የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌ የሚቃረን፤ ሕጉን ያለአግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ የሚጠቅስ፤ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ከጉዳዩ ጋር የማይዛመድ ጭብጥ ተይዞ ከተወሰነ፤ በዳኝነት ሊታይ የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ ማድረግ፤ በፍርድ አፈፃፀም ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ ተሠጥቶ ከሆነ፤ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ሳይኖረው ከተወሰነ የአስተዳደር አካላት ከሕግ ውጪ ያሳለፉት ውሳኔ ካለ ወይም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔን በመቃረን የተወሰነ ከሆነ እነኚህ መሠረታዊ የሕግ ስህተቶች ናቸው። ስለዚህ እነኚህ ውሳኔዎች የሚነሱበት ሁኔታ ካለ ወደ ሰበር ሊሄድ እና አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ ሊሰጥበት ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡-መቅረብ ያለበት በምን መልኩ ነው?**

**አቶ አሮን፡-** መቅረብ ያለበት እና መዳኘት ያለበት ሲባል እስከ አሁን ከላይ እንደጠቀስኩት ምንም ዓይነት የሥነሥርዓት ሕግ ስላልነበረ ፍርድ ቤቶቻችን በተለይም ሰበር ሰሚ ችሎት በመደበኛው የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕግ እየተጠቀሙ ይዳኙ ነበር። ነገር ግን አሁንም አዋጅ 1234 ስለሰበር አቀራረብ በተመለከተ አዲስ ያመጣው ፅንሰ ሃሳብ አለ። በተለይ ከአንቀፅ 27 ጀምረን ስናነበው በአንቀፅ 28ም የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነሥርዓት ምን መምሰል አለበት? አቤቱታ ሲቀርብ የሚያዩት ችሎቶች እነማን ናቸው? የሚታየው በምን መልኩ ነው? የሚለውን መርሆቹን ያስቀምጥ እና ዝርዝር አፈፃፀሙን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ይላል።

የሰበር አቤቱታን የሰበር ችሎቱ የሚያየው በምን መልኩ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 2588 እና እርሱን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ 454/1987 ዓ.ም መጀመሪያ ሦስት ዳኞች ለተሰየሙበት ችሎት ይቀርባል። እነዛ ሦስት ዳኞች ጉዳዩን ያዩ እና ለዋናው ሰበር ችሎት የሚያስቀርብ የሚያጠራጥር ነጥብ አለው ወይስ የለውም ብለው ያጣራሉ። በተለምዶ አጣሪ ችሎት ተብለው ይጠራሉ። ወደ ዋናው ችሎት ሔዶ መታየት አለበት ብለው ካመኑ ወደ ዋናው ሰበር

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ወቅታዊ

# ‹‹መመሪያው የሰበር ውሳኔዎች አጠቃላይ ሒደት ግልፅ...



**ከገጽ 10 የዞረ**

ችሎት ይመሩታል። ይህ በሕጉ የተቀመጠ ነው።

በሕግ ቢቀመጥም በተግባር ግን ይደረግ የነበረው ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል አያስቀርብም፤ ለማለት በሥነሥርዓቱ ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ሳይጠሩ ጭብጥ ያወጡና መርምረው መቅረብ አለበት ካሉ ይመራል። አያስቀርብም ያሉበትን ምክንያት ሳይገልፁ መቅረብ የለበትም ብለው ዝም ብለው ይዘጉታል። ይህ ግን በዚህኛው አዋጅ ቀርቷል።

አሁን ሦስት ሂደቶች ይኖሩታል። አንደኛው ሦስት ዳኞች ለተሰየሙበት ለአጣሪ ችሎት ይቀርባል። ምንም ጭብጥ መመስረት አያስፈልገውም፤ አጣሪ ችሎቱ አይቶ ለዋናው ሰበር ችሎት ይመራዋል። ዋናው ሰበር ከአጣሪ ችሎቱ የመጣለትን አይቶ አዎ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ ነገር አለ ብሎ ካመነ ለተጠሪ መጥሪያ ይልካል፤ ሦስተኛው ሂደት ላይ አዳምጠው ምንም የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም ወይም አለ ብለው የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣሉ። ይህንን ዝርዝር አካሔድ አሁንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል ይላል። በዚህ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚያዝያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም የሰበር መመሪያ አውጥቷል።

መመሪያ ቁጥር 17 በሚል የወጣው መመሪያ ተፈፃሚ መሆን የጀመረው ሚያዝያ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ነው። ይህ 15 ቀን የዝግጅት ጊዜ የጠየቀ ሲሆን፣ ከትግራይ ክልል ውጪ ላሉ ለ10ሩም ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች እና ለፍትሕ ቢሮዎች፤ ለሁለቱ ከተማ መስተዳድር ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለፍትህ ቢሮዎች ተልኳል። እንዲሁም ለፍትህ ሚኒስቴር፣ ለጠበቆች ማህበር እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ተልኳል።

በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 80 ንዑስ ቁጥር 3 ፊደል ተራ ሀ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአገሪቱ በማናቸውም አካል የተሰጠ ውሳኔን በሰበር የማየት ሥልጣን እንዳለው ያስቀምጣል። የክልልንም ጨምሮ ማለት ነው። ይህ በእርግጥ ከፌዴራል ሥርዓት አወቃቀር ጋር የሚሔድ አይደለም። የሚል ተቃውሞ ይቀርብበታል። ምክንያታቸው ክልሎች የራሳቸው ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ አካል አላቸው። ሕግ ተርጓሚው ደግሞ የየራሱ ሰበር ሰሚ አለው፤ ነገር ግን በሰበር ሰበር ጉዳያቸው ወደፌዴራል ይመጣል። ይህ ፌዴራላዊ ሥርዓቱን ይቃረናል በሚል የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ይጠየቃል። እኛም እናምናለን፤ አንደኛ ለፌዴራል ፍርድ ቤቱ ጫና ነው። ሁለተኛ ከፌዴራል ሥርዓቱ ጋር መሔድ አለበት። ነገር ግን ሃሳቡን ብናምንበትም ሕገ-መንግሥቱ እስኪሻሻል ድረስ ዞሮ ዞሮ ግን የምንሠራው በተፃፈው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እዚህ ላይ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እና የራሳቸው ሕግ ተርጓሚ ቢኖራቸውም ከእነርሱ አልፎ ወደ ፌዴራል ፍርድ ቤት ቢመጣ ያሉት በአንድ አገር ውስጥ ነው፤ ችግሩ ምንድን ነው?**

**አቶ አሮን፡-** ክልሎች በክልላቸው ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣሉ። ምናልባት አንድ አገር ነው። የክልል ሕገ-መንግሥቶች ቢኖሩም አንድ የፌዴራል ሕገ-መንግሥት አለን። ስለዚህ ለምን በዛ አንዳኝም ከተባለ ምናልባት ክልሎች ሕገ-መንግሥትን የሚቃረን ውሳኔ ከሰጡ ሕገ-መንግሥትን የሚያስነሳ ጉዳይ ከመጣ ወደ ሕገ-መንግሥታዊ አጣሪ ጉባኤ መቅረብ ይችላሉ። ይህ የማይነካ መብታቸው ነው። ነገር ግን በሰበር የሚታየው ጉዳይ ግልፅ የሕግ ክርክር ነው። ሌላው ቀርቶ ሰበር ሰሚው ራሱ ሕገ-መንግሥታዊ መብቴን ጥሷል ብሎ አቤቱታ አቅራቢ የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይሔዳል። ይህ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ ያለው የሕገ-መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ግን የመጨረሻው ውሳኔ ነው። ክልሎችም ይህን ማድረግ ይችላሉ። ይህኛውን እኔ ያልኩት ከፌዴራል አወቃቀር አንፃር ነው። የራሳቸውን የሰበር ችሎት ማቋቋም በተመለከተ ትርጉሙ ምንድን ነው? ብለው ጥያቄ የሚያቀርቡ አሉ። ከሕግ ተርጓሚው ጋር አብሮ የማይሄድ ከሆነ ትርጉም የለውም የሚሉ አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የፍትሐብሔርም ሆነ የወንጀል ሕግ ተቀርፃ ሰበርም እየተቋቋመ የሕግ ውሳኔዎች መተሳሰፍ ከጀመሩ ከ60 ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል። እንዴት እስከአሁን የሰበር የሥነሥርዓት መመሪያ አልተዘጋጀም? አስፈላጊ ካልሆነ ለምን እስከአሁን ሲሠራበት እንደነበረው አልቀጠለም?**

> **‹‹መሠረታዊ የሕግ ስህተት ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የሕግ ስህተት ያለበትን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10 መሠረት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲታዩ የሚችሉ የመጨረሻ ውሳኔ ፍርድ ብይን ትዕዛዝ ማለት ነው››**

**አቶ አሮን፡-** በመሠረቱ ሕገ-መንግሥቱ በ1987 ዓ.ም ኅዳር ላይ ፀድቆ ነሐሴ ላይ ተግባራዊ መሆን ሲጀምር በሕገ-መንግሥቱ በተቀመጠው መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ጨምሮ የፌዴራል ተቋማት ተቋቁመዋል። ከሕገ-መንግሥቱ መፅደቅ በፊት ማዕከላዊ ጠቅላይ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይባሉ ነበር። የወረዳ እና የአውራጃ ፍርድ ቤቶች ነበሩ። ይህ በሽግግር ጊዜም ሆነ በደርግ ጊዜ የነበረ አወቃቀር ነው። ሕገመንግሥቱ ከፀደቀ በኋላ ግን የወረዳ የአውራጃ የሚለው በአንድ ላይ ተጨፍልቆ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ ማዕከላዊ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የነበረውን ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም ማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤትን ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብሎ አደራጀ።

ነገር ግን ሰበርን በተመለከተ ግልፅ በሆነ መልኩ፣ የሚሰጣቸውን ውሳኔዎችም ራሱ አስገዳጅ መሆናቸውን፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ደግሞ እነዚህን አስገዳጅ የሰበር ውሳኔዎች እያሳተመ ማሰራጨት አለበት፤ እያለ መደንገግ የጀመረው መጀመሪያ በአዋጅ ቁጥር 25 በ1988 ቀጥሎ በአዋጅ ቁጥር 454 በ1997 ነው። እርሱም ቢሆን ግልፅ በሆነ መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነሥርዓት መመሪያ ማውጣት እንደሚችል አላስቀመጠም። በእርግጥ በአዋጅ ቁጥር 454 በ1997 ላይ ሰበርን በተመለከተ የሥነሥርዓት አካሔድ እንደሚኖረው ያስቀምጣል። እርሱም ራሱ ግልፅነት ይጎድለው ነበር። እናም እስከ አሁን አልወጣም።

ነገር ግን መመሪያው እንዲወጣ በርካታ ግፊቶች ነበሩ፤ ዳኞችም በጣም ይቸገሩ ነበር። መውጣት አለበት ይላሉ። የሕግ ባለሙያዎችም ባለጉዳዮችም ጠበቆችም ግፊት ያደርጉ ነበር። ነገር ግን ሳይወጣ በመቆየቱ የሚመጡት ችግሮች እየሰፉ እና እየጠነከሩ በመምጣታቸው የሰዎችን የመሰማት፣ ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት የማግኘትን መብት እየነካ ለቅሬታ ምንጭ እየሆነ ፍርድ ቤቶች ለትችት ሲዳረጉ በተለይ አዲስ አመራር ከመጣ ከአራት እና ከአምስት ወር ወዲህ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል በሚል ተሠርቷል። አዲስ አዋጅም 1234 የወጣ በመሆኑ እና እርሱም ስለሚያስገድድ መመሪያው እንዲወጣ ሆኗል። ይህ የኅብረተሰቡን የፍትህ ጥያቄ ለመመለስ ይህ መመሪያው አስፈላጊ በመሆኑ በከፍተኛ ርብርብ መመሪያው ወጥቷል። ነገር ግን በፊት ትኩረት ባለመስጠት እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ቢሆንም፤ አሁን አዋጅ 1234 በመምጣቱ ውጤት የሆነው ይህ መመሪያ መጥቷል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲሱ መመሪያ ዋነኛ ይዘት ምንድን ነው?**

**አቶ አሮን፡-** ይዘቱ በአራት ዋና ዋና ክፍሎች እና በሃያ ሁለት ድንጋጌዎች የተደራጀ ነው። አላማውን ስንመለከት በመመሪያው የመጀመሪያ ክፍል በመግቢያው ላይ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በጠቅላላ፤ ፌዴራል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ በተለይ ጉዳዮችን በሰበር አይቶ አስገዳጅነት ያላቸው ውሳኔዎችን እና አስገዳጅነት ያላቸውን የሕግ ትርጉም የመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶታል። ነገር ግን ይህንን ሥልጣኑን ተግባራዊ ሲያደርግ መከተል ያለበት ሂደት ምን መልክ መያዝ አለበት። የሰዎችን መብት እና ፍላጎት የሚያስጠብቀው እንዴት ነው በሚል በግልፅ እና በዝርዝር መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ መመሪያው መዘጋጀቱ ተገልጿል። ሌላው የሰበር ውሳኔዎችም ሆኑ አጠቃላይ ሒደቱ ግልፅ እና ቀልጣፋ መሆን አለበት። ሊተነበይ የሚችል ውጤታማ ውሳኔዎች እንዲሰጡ ሥርዓት መዘርጋት ስላለበት መመሪያው ተዘጋጅቷል።

በመጀመሪያ ደረጃ የሰበር አቤቱታ መረጃ የሚዘጋጀው እንዴት ነው የሚል ጥያቄ ሲነሳ ከላይ እንደጠቀስኩት የሰበር አቤቱታ ማመልከቻ ይዘት ምን መምሰል አለበት የሚለውን በዝርዝር መመሪያው ያስቀምጣል። ለምሳሌ በመመሪያው አንቀፅ 4 ላይ የሰበር አቤቱታ ይዘት ምን መምሰል እንዳለበት ተዘርዝሯል።

በማንኛውም ክስ በመደበኛውም ሆነ በወንጀል ክስ የጥያቄው አቀራረብ ምን ይመስላል ከተባለ፤ የከሳሽ እና የተከሳሽ ስም፣ አድራሻቸው፣ የፍርድ ቤቱ ሥልጣን እና አጠር ባለ መልኩ ጭብጡ ይቀርባል። ይህ በመደበኛውም ክርክር ያለ ነው። ልክ እንደዚያው የሰበር አቤቱታም ምን መምሰል እንዳለበት ያስቀምጣል። ለምሳሌ የአመልካች እና የተጠሪ ሙሉ ስም እና አድራሻ፣ የመጨረሻ ውሳኔ፣ የተሰጠው ውሳኔ የመዝገብ ቁጥር፣ አግባብነት ያለውን የአቤቱታ መነሻ ነጥብ በአጭሩ፣ አመልካቹ ለአቤቱታው መሠረት የሆነው ተፈፅሟል የተባለው መሠረታዊ የሕግ ስህተት እና በአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 4 ከ‹ሀ› እስከ ‹ሸ› እና አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 1 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል ማለትም ሕገ-መንግሥቱን የጣሰ ነው። የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረው የታየ ነው፤ ወይም የፍርድ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባው ጉዳይ ውድቅ ተደርጓል፤ የመሰማት መብቴ ተጥሷል የሚባል ከሆነ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ወይም ሁለቱ የተፈፀመ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈፅሟል ሊያሰኝ የሚችለው ጉዳይ በአጭሩ ይገለፃል። በመጨረሻም ከሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት የሚፈልገውን ውሳኔ ይጠይቃል። ካሳ የከፈለኝ ሊሆን ይችላል።

ይህ ማመልከቻ የሚቀርበው ለየትኛው ችሎት ነው? የቀረበለት ችሎትስ የሚያስተናግደው በምን መልኩ ነው? የሚለው በክፍል ሦስት ቀርቧል። የሰበር አቤቱታ አቀራረብ እና የክርክር አመራር ይላል። የሰበር አቤቱታ የሚቀርብበት ሥነሥርዓት ብሎ የሰበር አቤቱታ ለሰበር ችሎት የሚቀርበው እና የሚሰማው፤ በአዋጁ አንቀፅ 28 ንዑስ ቁጥር 1 መሠረት አቤቱታው አስቀድሞ የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታ የቀረበበትን የእስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በአዋጁ አንቀፅ 2 ንዑስ ቁጥር 4 እና በአዋጁ አንቀፅ 10 ንዑስ ቁጥር 1ስር ከተመለከተው ምክንያቶች አንፃር በሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወስን ብቻ ነው።

ስለዚህ መጀመሪያ ለአጣሪ ችሎቱ ይቀርባል። አጣሪ ችሎቱ ደግሞ አቤቱታው በየትኛው ስር ይወድቃል ብሎ አቤቱታው ትክክል ነው ወይ ብሎ ያጣራል። ለምሳሌ ሕገመንግሥታዊ መብቴ ተጥሷል ከተባለ በትክክል ሕገመንግሥታዊ መብት ተጥሷል ወይ ተብሎ ወይም መጣሱን የሚሳይ ምልክት አለ ወይ ወይም የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖረው የእስር ፍርድ ቤቱ ወሰነብኝ ቢሉም በትክክል በዚህ ላይ ያለውን በመጀመሪያ አጣሪ ችሎቱ ያያል። ከዚያ በኋላ በዚህ አንቀፅ 1 ሥር በተደነገገው መሠረት የሰበር አጣሪ ችሎቱ መርምሮ ከመወሰኑ በፊት አመልካቹን ጠርቶ መስማት አለበት ይላል። ይህ መሠረታዊ የሆነ የመሰማት መብት ነው። ስለዚህ በቀረበው ማመልከቻ ላይ ብቻ ተመስርቶ ያስቀርባል አያስቀርብም ብሎ ውሳኔ ማስተላለፍ ቀርቷል ማለት ነው።

በተጨማሪ አጣሪው እንደበፊቱ በደፈናው በፎርም ለሰበር ውሳኔ መቅረብ ይችላል ወይም አይችልም ከማለት ይልቅ ምክንያቱ እንዲብራራ ያስገድዳል። የዳኝነት ውሳኔ ምክንያታዊ መሆን አለበት። ትክክል ነው አይደለም የሚለው በዝርዝር በምክንያት ማስቀመጥ አለበት። ይህ ለሰበር ብቻ ሳይሆን ለይግባኝም ችግር ሆኗል። የይግባኙ ግን የፍትሐብሔር ሥነሥርዓት ሕጉ ሲሻሻል አብሮ የሚታይ ይሆናል።

ሌላው የሰበር ችሎት ክርክር አመራሩ የሚታየው በምን መልኩ ነው? የሚለውም በዚሁ በክፍል ሦስት ላይ ያስቀምጠዋል። ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከአጣሪ ችሎቱ የመጣውን አይቶ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ሲሰጥ ተጨማሪ ማጣሪያ ከፈለገ አቤቱታ አቅራቢውን አስቀርቦ ማነጋገር ይችላል፤ በተጨማሪ ተጠሪውንም በማስቀረብ ጭብጥ አውጥቶ ማከራከር ይችላል፤ ይላል።

ተጠሪው መልስ የሚያዘጋጅበት ሂደት በመመሪያው ተቀምጧል። መልስ ብቻ ሳይሆን የመልስ መልስም ዕድል ይሰጣል። በመጨረሻም የሰበር ችሎቱ ሥልጣን ምንድን ነው ለሚለውም በዚሁ ክፍል አንቀፅ 9 ላይ የሰበር ችሎትን ውሳኔ የማፅናት፣ የማሻሻል፣ የመለወጥ ወይም ሙሉ ለሙሉ የመሻር ሥልጣን አለው። ይህ አምስት ዳኞች የተሾሙበት ማለት ነው። በዚህ መሠረት መመሪያው የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ የቀረበ ሲሆን፣ ለመደበኛው የፍርድ ቤት አካሔድም ዓይን ገላጭ የሆነ ጥቅም ያለው የፍትህ ዘርፉን የሚያግዝ ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ።**

**አቶ አሮን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ



## የሱዳን ጦር፣ የሄሜቲ ጦር ተጨማሪ ኃይል ከዳርፉር ወደ ካርቱም እያንቀሳቀሰ ነው ሲል ከሰሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሱዳን ጦር፣ በጀነራል ሀምዳን ደጋሎ ወይም ሄሜቲ የሚመራው ፈጥኖ ደራሽ ኃይል ከዳርፉር ግዛት ተጨማሪ ኃይል ወደ ካርቱም እያንቀሳቀሰ ነው ሲል ከሷል። ተፋላሚ ኃይሎቹ በሳኡዲ አረቢያ ለመነጋገር ስምምነታቸውን መግለጻቸው ይታወሳል።

ጦሩ ከዚህ በተጨማሪም የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች የንግድ ባንኮችን በመዝረፍ ላይ ተሳትፏል ሲልም ወንጅሏል። ጦሩ ከዚህ በተጨማሪም የፈጥኖ ደራሽ ኃይሎች የንግድ ባንኮችን በመዝረፍ ላይ ሲልም ወንጅሏል።

በቀረበበት ክስ ዙሪያ ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ የተናገረው የለም። በሱዳን አጋር በነበሩት ሁለቱ ጀነራሎች መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት ሶስት ሳምንታትን አስቆጥሯል።

ጦርነቱ ሲጀመር አንስቶ ሁለቱ ኃይሎች ተኩስ እንዲያቆሙ ጫና ቢደረግባቸው በተለያየ ጊዜ የገቧቸውን የተኩስ አቁም ስምምነቶች ተግባራዊ ማድረግ አልቻሉም። በከፊል ተግባራዊ ሆኖ የነበረው ተኩስ አቁም በአሜሪካ እና ሳኡዲ አረቢያ አማካኝነት የተደረሰው ተኩስ አቁም ስምምነት ነበር።

በሳኡዲ እና በአሜሪካ የተደረሰው ተኩስ አቁም ለሰባት ቀናት እንዲራዘም የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ሁለቱን ተፋላሚ ኃይሎች ማስማማታቸውን ቢገልጹም በድጋሚ ጦርነቱ ቀጥሎ ነበር። ካርቱም እና ሌሎች ቦታዎች በታንክና መድፍ ድምጾች ሲናወጡ ነበር።

ተፋላሚ ኃይሎቹ በሳኡዲ አረቢያ ለመነጋገር ስምምነታቸውን መግለጻቸው ይታወሳል። በሱዳን ጦርነት ምክንያት በርካቶች ሲገደሉ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ደግሞ ወደ ጎረቤት ሀገራት ተሰደዋል፤ በመሰደድም ላይ ናቸው ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።

## ኡጋንዳ ከሌባ ላይ ሰርቀዋል

### የተባሉ 10 ፖሊሶችን በቁጥጥር ስር አዋለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኡጋንዳ ከሌባ ላይ ሰርቀዋል የተባሉ 10 ፖሊሶችን በቁጥጥር ስር አዋለች።



ኡጋንዳ ከሌባ ላይ ሰርቀዋል የተባሉ 10 ፖሊሶችን በቁጥጥር ስር የዋሉት የተያዙት ከሌቦች የያዙትን የገንዘብ መጠን አሳንሰው አቅርበዋል በሚል ነው ተጠርጥረው የተያዙት።

ኡጋንዳ ከሌባ ላይ ሰርቀዋል ያለቻቸውን 10 ፖሊሶች በቁጥጥር ማዋሏ ተገልጿል። የኡጋንዳው ዴይሊ ሞኒተር ጋዜጣ እንደዘገበው፤ ፖሊሶቹ ከሌቦቹ የያዙትን የገንዘብ መጠን አሳንሰው አቅርበዋል በሚል ነው ተጠርጥረው የተያዙት።

መርማሪዎች እንደገለጹት፤ ሶስት ሰዎች ሞተር ሳይክል በመጠቀም ከውጭ ምንዛሬ ቢሮ ሲወጣ ከነበረ ግለሰብ ላይ 110 ሺህ ዶላር ወይም 407 ሚሊዮን ሽልንግ ሰርቀዋል።

የካምፓላ ፖሊስ፣ 407 ሚሊዮን ሽልንግ በመስረቅ ከተጠረጠሩት ሌቦች ላይ 146 ሚሊዮን ሽልንግ ሰርቀዋል ያላቸውን 10 ፖሊሶች በቁጥጥር ስር አውሏል።

የኡጋንዳ ፖሊስ በቅርቡ ህገወጥ የሆነ ሰልፍ አካሂደዋል በሚል 11 የምክር ቤት አባላትን አስሮ ነበር። በተወሰኑ የምክር ቤቱ አባላት ላይም ጉዳት ደርሶባቸው ነበር።

የምክር ቤት አባላቱ በፖሊስ የተያዙት በካምፖላ ከሚገኘው ፓርላማ ዙሪያ ተነስተው ተቃውሟቸውን ወደ ሀገር ውስጥ ሚኒስቴር ለማሰማት ሲሄዱ በነበረበት ወቅት ነው ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው።


# ግልጽ ጨረታ የማስታወቂያ


የደብረብርሃን ኮፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በ2015 በጀት ዓመት ለሆስፒታሉ አገልግሎት የሚውል ኤሌክትሮኒክስ እቃ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**በዚሁ መሰረት፡-**

- በዘመኑ(በ2015 በጀት ዓመት) የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ቲን ነበር ያላቸው ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ፈቃድ ያላቸው ተጫራቾች መሳተፍ ይችላሉ፡፡
- የግዥ መጠኑ 200,000.00 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እና በላይ ከሆነ ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል ከሆስፒታሉ የእለት ገንዘብ ቤት መግዛት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች ለሚሳተፉበት ጨረታ ህጋዊ ፣ ተቀባይነት እና አግባብነት ያለው ፍቃድ ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ከላይ የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች የመጫረቻ ሰነዳቸውን ኦርጅናሉን ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ኤሌክትሮኒክስ እቃ አይነትና የስራ ዝርዝር መሰረት የጨረታ ሰነዱን ዋጋ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች በሆስፒታሉ በቀረቡት ኤሌክትሮኒክስ እቃ አይነትና የስራ ዝርዝር መሰረት የጨረታ ሰነዱን ዋጋ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ሁሉም ተጫራቾች በያንዳንዱ የስራ ዝርዝር እና የተጫራቾች መመሪያ መሠረት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው።
- ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ጨረታ በሆስፒታሉ የጨረታ ሰነድ አይነት እና ዝርዝር (እስፔስፊኬሽን) መሰረት ማቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች የሚያቀርቡትን እቃ የተመረተበትን ሀገር እና ብራንድ በጨረታ ሰነዱ ላይ መጥቀስ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች የሚያቀርቡትን ኤሌክትሮኒክስ እቃ ጥራት ያለው እና አንደኛ ደረጃ ሆኖ በገበያ ላይ ተመራጭ መሆን አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች ያሸነፉበትን _ኤሌክትሮኒክስ እቃ ከማቅረባቸው በፊት ናሙና በማቅረብ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በራሳቸው ወጪ በማቅረብ ለሆስፒታሉ ንብረት ክፍል ማስረከብ አለባቸው፡፡ ሆስፒታሉ የእቃውን ጥራት እና በናሙናው መሰረት የቀረበ መሆኑን በሚመለከታቸው ባለሙያዎችና ኃላፊዎች በማረጋገጥ ይረከባል፡፡
- ባሸነፉበት ጥራትና ዋጋ ዝርዝር መሰረት ልዩነት ቢኖረው እና የጥራት ችግር ቢከሰት በራሳቸው ወጪ እንደገና የመተካት እና የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች ያሸነፉበትን እቃ ናሙና ሳያቀርቡ ሙሉ ለሙሉ ይዘው ቢመጡና እቃው ተፈላጊ አይነት ሳይሆን ቢቀር ሙሉ በሙሉ ወዲያውኑ መልሰው በራሳቸው ወጪ አቅርበው በናሙናው መሰረት መሆኑ ሲረጋገጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች በተጫራቾች መመሪያ ላይ የተቀመጠውን ህግ ማክበር አለባቸው፡፡ ጨረታ ከመከፈቱ በፊት የተወዳደሩበትን ዋጋ ቫትን ጨምሮ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) 50,0000 (ሃምሳ ሺህ ብር) የጨረታ ማስከበሪያ በማስያዝ እና ካሸነፉ በኋላ ያሸነፉበትን ዋጋ የውል ማስከበሪያ 10% በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትእዛዝ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ በባንክ ዋስትና ወይም በጥሬ ገንዘብ ሆ/ሉ ገንዘብ ቤት ድረስ ማስያዝ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች አሸናፊነታቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5 ቀን ውስጥ የውል ማስከበሪያ ያሸነፉባቸውን ጠቅላላ ዋጋ 10% በማስያዝ በውልና ማስረጃ ውሉታ በማስፈፀም መቅረብ አለባቸው፡፡
- ተጫራቾች ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ለ 15 ቀናት አየር ላይ ቆይቶ በ 16ተኛው ቀን 4፡30 ድረስ የጨረታ ሰነዱን ሞልተው ማስገባት ይችላሉ፡፡ የጨረታ ሳጥኑ ወዲያውኑ ይታሸጋል፡፡ በ16ተኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ይከፈታል፡፡ እለቱ የበአላት ቀን ከሆነ በቀጣይ የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰአት ይከፈታል፡፡
- የጨረታ ሰነዱ ጨረታ ከተከፈተ በኋላ 40 ቀናት ፀንቶ ይቆያል፡፡
- ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ በግዥ ፋ/ንብ/አስ/ቡድን ቢሮ ድረስ በአካል በመገኘት፣ በስልክ ቁጥር 0116813390 ወይም በፋክስ 0116811008 ቁጥር በመላክ መጠየቅ ይቻላል፡፡
- መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ይሁን በሙሉ የመሰረዝ መብቱ እንዲሁም ግዥውን በጥቅል ፣ በተናጠል ወይንም በሌላ የተሻለ መንገድ አወዳድሮ የመግዛት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**የደብረብርሃን ኮም/ስፔ/ ሆስፒታል**

# ስፖርት



# በስፖርት ዘላቂ ውጤት ለማስመዝገብ ጥናት እየተዘጋጀ ነው

**ብርሃን ፈይሳ**

በውድድር ውጤታማነት ብቻ ስኬታማ መባል እንደማይቻል ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለዚህም ማሳያ የሚሆነውም በአንድ ስፖርት ቋሚና ቀጣይነት ያለው ውጤት አለመገኘቱ ነው። ለአብነት ያህልም ኢትዮጵያ ውጤታማ በሆነችበት አትሌቲክስ፤ በአንድ ዓመት ልዩነት በተካሄዱት የቶኪዮ ኦሊምፒክ እና የኦሪገን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የተመዘገበውን ውጤት ሰፊ ልዩነት ማንሳት ይቻላል። በአህጉር አቀፍ ውድድሮች በዓመታት ልዩነት የሚገኝ የእግር ኳስ ስፖርት ተሳትፎንም ለአብነት ማንሳት ይቻላል።



ቀጣይነት ያለው ውጤት በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ አለመመዝገባቸው በኢትዮጵያ ስፖርት ከሚታዩ ክፍተቶች መካከል አንዱ ነው። በመሆኑም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር በዚህ ላይ የሚያተኩርና የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚያመላክት ጥናት በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ጥናቱም ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስፖርት ሳይንስ መምህራን፣ ከስፖርት ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ ከመገናኛ ብዙኃን እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተውጣጡ 17 ባለሙያዎችን ባካተተ ቡድን እየተከናወነ ይገኛል።

በዚህም በስፖርቱ ወጥ የሆነ ውጤታማነት ላለመመዝገቡ ምክንያቱ ምን ምንድነው በሚል፤ ለስኬታማነትስ ተግዳሮት የሆነው የዝግጅት፣ የስልጠና ግብዓቶች፣ ድጋፍ አለመኖር፣... የሚለውን ለይቶ ለማውጣት እንደሚቻል በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ በቀለ አመላክተዋል። ከጥናቱ ከሚገኘው ግብረመልስ ባለፈም ባለድርሻ አካላትን በመጋበዝና ግብዓት የሚሆኑ ሃሳቦችን በማካተትም ስትራቴጂክ እቅድ ይዘጋጃል።

በተጨማሪም ጥናቱ ተለይተው በተመረጡ ስፖርቶች እንዴት ውጤታማ ለመሆን ይቻላል የሚለውንም ያካተተ መሆኑን ሥራ አስፈጻሚው ጠቁመዋል። እነዚህ ስፖርቶችም አትሌቲክስ፣ እግር ኳስ፣ ቮሊቦል፣ ጠረጴዛ ቴኒስ፣ ወርልድ ቴኳንዶ እና ብስክሌት ናቸው። በእነዚህ ስፖርቶችም እንደ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ማድረግ ብቻም ሳይሆን ውጤት ማስመዝገብ እንዲቻል ታስቦ ነው ጥናቱ የሚካሄደው።

በዓለም አቀፍ ውድድሮች ውጤታማ ለመሆን ከጥናቱ ባሻገር በቅድሚያ የሚከናወኑ በርካታ ተግባራት ይኖራሉ። ዋነኛው ተግባር ተመጋጋቢነት ያለው ሥልጠና ሲሆን፤ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ደግሞ ለሁሉም መሠረት ነው። በመሆኑም ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በተያዘው ዓመት በአዲስ መልክ በ1ሺ269 የሥልጠና ጣቢያዎች ላይ 31 ሺ የሚሆኑ ታዳጊዎችን በ11 የስፖርት ዓይነቶች ለማሠልጠን አቅዶ ነበር። ይሁንና እስካሁን 96 በሚሆኑ ጣቢያዎች ላይ 18ሺ የሚሆኑ ታዳጊዎች ናቸው ወደ ሥልጠና የገቡት።

ይህንንም በመመልከት የሚገመግም በሦስት የተከፈለ ልዑክ በቅርቡ ወደየአካባቢው የሚጓዝ ይሆናል። ይህን በማድረግም ከዚህ ቀደም እንዳጋጠመው ውድቀትን በመጨረሻ ከማመላከት ይልቅ ሂደቱ ምን ይመስላል የሚለውን ለመመዘን እንደሚያስችልም ሥራ አስፈጻሚው ይጠቁማሉ። በሌላ በኩል በመላው አገሪቷ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚና የጥሩነሽ ዲባባ ማሰልጠኛ ማዕከልን ጨምሮ በጠቅላላው 19 የማበልጸጊያ ማዕከላት ያሉ ሲሆን፤ ግማሽ በሚሆኑት ላይ በባለሙያዎች ምልከታ ተደርጓል። በዚህም ሥልጠናው ምን ይመስላል፣ በምን መልክ ይሰጣል፣ በእርግጥም በሪፖርት ከሚቀርበው ጋር ተመሳሳይ ነው የሚለውን መገምገም እንዲሁም ችግሮቻቸውን ነቅሶ ማውጣት ተችሏል።

በዚህ ግምገማም የተደረሰበት በማበልጸጊያ ማዕከላቱ የሚሰጠው ሥልጠና ተመሳሳይ አለመሆኑ ነው። የሥልጠና አሰጣጡ፣ ሥልጠናው የሚሰጥበት ጊዜ ቆይታ፣ የማሠልጠን ብቃት፣ ወደ ማዕከላቱ ተመርጠው የሚገቡ ሠልጣኞች ያላቸው ተክለ ቁመና፣ ... የተለያየ መሆኑ ተረጋግጧል። በተለይ በክልል ያሉ ማዕከላት የተለያየ የገቢ ምንጭ ያላቸውና የብቃታቸውም ልክ የማይገናኝ ነው። በመሆኑም የተገኘውን መረጃ በመተንተንና የአማራጭ ሃሳቦችን በመያዝ የግንዛቤ መስጫ መድረክ ለማዘጋጀት በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል። ከዚህ ጎን ለጎን መልካም ልምድ ያላቸው ማዕከላት ተሞክሯቸውን ለሌሎች እንዲያካፍሉ ለማድረግ መታቀዱንም ሥራ አስፈጻሚው ጨምረው ገልጸዋል።


# የጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን እቃዎች እና አገልግሎቶች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት/ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

**የግዢው መለያ ቁጥር፡- BOHEA-PPAD-NCB-REC-Budget-2015**

| ምድብ | የዕቃው አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|---|
| ሎት አንድ | ጀነሬተር 40 KVA Delivery, Supply and full Installation | 60,000.00 |
| ሎት ሁለት | የአይ ቲ ማቴሪያል እና ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች | 200,000.00 |
| ሎት ሶስት | ሊፍሌት ዲዛይን፣ ብሮሸር ዲዛይን፣ የቴሌቪዢን ስፖት ማዘጋጀት ብሎም የተዘጋጀውን ሊፍሌት እና ብሮሸር ህትመት | 10,000.00 |

1. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር የከፈሉና ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የቫት ተመዝጋቢ ሆነው ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉና መለያ ቁጥር ቲን ነበር ያላቸው መሆን አለበት፡፡
3.ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸውና በዘርፉ የተሰማሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ከላይ የተጠቀሰውን ብር በየሎቱ ለየብቻ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
5. የጨረታ አሸናፊዎች አሸናፊነታቸው ከተገለፀ በኋላ ያሸነፉበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት 10% የውል ማስከበሪያ /ሲ.ፒ.ኦ/ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ቦንድ ማስያዝ አለባቸው፡፡
6. ተጫራቾች በግዥ አገልግሎት በአቅራቢነት ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት የሚያቀርቡ ብሎም በአሁኑ ሰዓት ያሉ መሆን አለባቸው፡፡
7. ተጫራቾች ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ብር 150 በየሎቱ በመክፈል ከመንግስት ግዢ ዳይሬክቶሬት እስከ 10ኛው ቀን ድረስ የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
8. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ እስከ 11ኛው የስራ ቀን 3፡45 ሰዓት ድረስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
9. መ/ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ የድርጅቱን ህጋዊ ማህተምና ፊርማ አድርጎ ያላቀረበ ተጫራች ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
10. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን የመጫረቻ ሰነድ ፋይናንስ ዋና እና አንድ ኮፒ እንዲሁም ቴክኒካል ዋና እና አንድ ኮፒ ለየብቻ በማድረግ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
11. ቢሮው በጨረታ ሰነዱ ከተገለጸው የዕቃ /የአገልግሎት ፍላጎት መጠን ጨረታ ሰነዱ ላይ ከውል በፊት 20% ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡
12. ጨረታው ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ 60 ቀናት ነው፡፡ አንድ ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፡፡
13. ጨረታው የሚዘጋበት ቀን የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣ በ11ኛው የስራ ቀን ጠዋት 3፡45 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ 4፡15 ሰዓት በመ/ቤቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተኙበት ይከፈታል፡፡ ይህ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ይሆናል፡፡
14. ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብት የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** መገናኛ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 71 ላንሴት ሆስፒታል ግቢ ውስጥ በጀርባው የሚገኝ ህንፃ 2ኛ ፎቅ የመንግስት ግዢ ዳይሬክቶሬት

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር ፡- 011-8-33-25-01 የመንግስት ግዢ ዳይሬክቶሬት**

**አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ**



# Invitation for Bids (NCB)

**Procurement of Construction of Ethiopian prosthetic and orthotic service**

**IFB** Number: -NCB/ 007/ 2015/

Invitation for Bids (IFB)

Procurement for Lot 1. Electrical Incinerator construction Work

Lott. Renovation Works Lot 3. Renovation and Expansion Works

- Ethiopian prosthetic and orthotic service invites sealed bids towards the cost for the Renovation of Electrical Incinerator construction Works, Renovation Works, Renovation and Expansion Works construction Work at Gefersa located center.
- Bidding will be conducted through the National Competitive Bidding (NCB) procedures specified in the Government Procurement Guideline.lnterested Bidders should fulfill the following requirements:
- This invitation is for all National Contractors having GC/BC-5 and above.
- Trade License on construction service License valid for the year - 2015 E.C.
- Ministry of Finance and Economic Development's registration certificate for the year -2015 E.C
- VAT registration certificate.
- Clearance from Inland Revenue Administration.
- Required Service:-for Electrical Incinerator construction Works, Renovation Works, Renovation and Expansion Works construction Work at Gefersa located center.
- Interested eligible bidders may obtain further information from Ethiopian prosthetic and orthotic service,+251-11-273-16-69 from 8:30 AM-12:30 AM and 1:30 PM -5:30 PM from Monday to Friday
- A complete set of Bidding Documents in English language may be purchased by interested bidders on the submission of a written Application to the address below and upon payment of a non refundable fee of Ethiopian Birr 500.00 (five hundred Birr)
- Bids must be delivered to the address below on or before 2:00 P.M on 21th calendar days beginning from the first date of advertisement on news paper. Electronic bidding will not be permitted. Late bids will be rejected. All bids must be accompanied by a Bid Security of lot 1-150,000 lot 2 100,000.00 birr lot 3 -100,000.00 birr and must be in the form of CPO or Bank Guarantee from any Bank of Ethiopia.
- Bids will be opened in the presence of the bidders' representatives, who choose to attend in person at the Finance and procurement Directorate at 2:30 P.M on the closing date.
- The Purchaser reserves the right to reject the bid fully or partially.

**Ethiopian prosthetic and orthotic service**